bes
bible educational services

# የመምህሩ መምሪያ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ደረጃ 1 እና 2

ሥርዓተ ትምህርት ለ
ለ1 - ለ 6

www.besweb.com

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት

በሕግ የተመዘገበ የዩናይትድ ኪንግደም ለጋሽ ድርጅት (የምዝገባ ቁጥር 1096157)

**ተልእኮ**

በአለም ዙሪያ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንዲሁም በዚህ ዘመን ያለውንና የወደፊቱን ትውልድ የእግዚብሔርን ቃል ለማስተማር የሚረዱ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በማዘጋጀት ሰዎችን ማገልገልና ለአገልግሎት ብቁ ማድረግ።

**ራዕይ**

የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አይነቶችን ስራ ላይ በማዋልና ዋና ዋና እሴቶቻችን ከሚጋሩ ግለሰቦች ጋር አብሮ በመስራት በተለየዩ የዓለም ቋንቋዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ዝግጅትን ማበረታታት።

## አጠቃላይ መረጃ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባራት ምንድናቸው?**

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት "ዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ"፣ "አዲስ ሕይወት" እና "ቃራሚዎች" በሚል ርዕስ የሚታወቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በእንግሊዝኛ ያሳትማል። እንዲሁም በምድረ እንግሊዝና በሌሎች የዓለም ክፍሎች በፖስታ ቤቶች አማካኝነት በመላላክ እነኝህን ትምህርቶች የሚሰጡ የርቀት ትምህርት ቤቶችንና ሌሎች ድርጅቶችን በጉብኝት፣ በምክር፣ በኔትወርኪንግና በስልጠና ያግዛል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በትርጉም፣ በዲዛይን፣ በሕትመትና ትምህርቶችን በማሰራጨት ከሚሰሩና በሌሎች አገሮች ውስጥ ከሚገኙ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሰራል። ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርቶቹ በነፃ እንዲዳረሱ ማድረግም ሌላው የመጽሐፍ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባር ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቶች በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉት በደቡብ አየርላንድ ከ50 ዓመታት በፊት ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በእንግሊዝኛና በሌሎች የውጭ አገር ቋንቋዎች የሚዘጋጁ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን የኤዲቶሪያል ኃላፊነት ይወስዳል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሕትመት በኤ 4 ፎርማት ሆኖ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በአራት ሳምንት አንድ ጊዜ ትምህርቶችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማዕከል ለእርማት መላክ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለቤት ለቤት ጀማ ወንጌል (የተሐድሶ ንቅናቄ) ምስጋና ይግባውና በቤልፋስት የ6 ወራት ትምህርቶች በኤ 5 ፎርማት ማዘጋጀት ተችሏል። ይህም ትምህርቶች በት/ቤቶችና በየአብያተ ክርስቲያናቱ በቀላሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስችሏል። ይህ ደግሞ ጥሩ የፖስታ አገልግሎት በሌለባቸው አካባቢዎች ውጤታማ ሆኗል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ኮርሶችን ልዩ የሚያደርጋቸው የቤት ለቤት ወይንም ደግሞ በቤተ ክርስቲያንና በት/ቤቶች የሚካሄዱ የቡድን ጥናቶችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተውና በሚገባ የታቀደ ሲለበስን ተከትለው ተማሪዎች ጥናታቸውን እድሜያቸው 20 ዓመት እስኪሆነው ድረስ እንዲቀጥሉ ስለ ሚረዷቸው ነው። ለየእድሜ ደረጃው የሚመጥኑ በአምስት ደረጃዎች የተከፋፈሉ ትምህርቶች ቀርበዋል። ቅድመ መደበኛ ትምህርት፣ ከ5-7 ዓመት፣ ከ8-10 ዓመት፣ ከ11-13 ዓመት፣ ከ14-16 ዓመት። ለእያንዳንዱ የእድሜ ክልል የሶስት ዓመት ሲለበስ ተዘጋጅቷል። (ገፅ አራትን ይመልከቱ።) እያንዳንዱ የእድሜ ክልል ባሉት ችሎታዎች መሠረተ ይለያያል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያጠኑ እድል ይፈጥርላቸዋል። ይህም የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንዲማሩና ወንጌልን በሕይወታቸው ለመተግበር በሚያደርጉት ጥረት የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች መጋፈጥ እንዲችሉ በማገዝ ነው።

የእነኝህ ትምህርቶች ኮፒዎች በእንግሊዝኛ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት (www.besweb.com) ላይ ማውረድ ይቻላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አብረውት በአጋርነት መስራት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚጠቅሙ ዶክሜንቶች አሉት። እነኝህ ዶክሜንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት ላይ ይገኛሉ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አድራሻዎች


**ዓለም አቀፍና የሰሜን አየርላንድ ፀሐፊ (የሁሉም ትምህርቶች አከፋፋይ)**
Mr S Balmer, 37a Belmore Street, Enniskillen, Northern Ireland BT74 6AA
ስልክ: 0286 632 2462
ኢሜይል: sam@besweb.com

**የዩናይትድ ኪንግደም ፀሐፊ**
Mr Stephen Gillham, 32 Firs Glen Road, West Moors, Ferndown, Dorset BH22 0ED
ስልክ: 01202 873500
ኢሜይል: stephen@sgilllham.co.uk

ዌብ ሳይት: www.besweb.com
የኢሜይል አድራሻ: info@besweb.com

## ለመምህራን መምሪያዎች

የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች በመጀመሪያ ሲዘጋጁ በፖስታ በመላላክ ለማስተማር ታስበው ነበር። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የፖስታ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ማዕከላት ተቋቁመው ነበር። ነገር ግን የፖስታ አገልግሎት አስተማማኝ ባልሆነባቸው እስከጭራሹንም እየቀረ በሚሄድባቸው ስፍራዎች በተለይም ደግሞ በአፍሪካና በሕንድ እንዲሁም በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለሚጠቀሙ የማስተማሪያ መምሪያዎችም ተዘጋጅተዋል። በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተዘጋጁት የመምህሩ መምሪያዎች ታሳቢ ያደረጉት ደረጃ 1 እና 2ን በግምት እድሜያቸው ከ5-10 ዓመት የሆኑ ልጆችን ነው።

እያንዳንዱ የመምህሩ መምሪያ ልክ በዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውስጥ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና መምሪያዎቻቸው በየሳምንቱ እንዲጠኑ ተደርገው ተዘጋጅተዋል። የሚያዚያ ትምህርቶች በተለይ ከፋሲካ ጋር የተገናኙ ትምህርቶች ሲሆኑ የታህሳስ ትምህርቶች ደግሞ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የተገናኙ ናቸው።

በአንዳንድ ቦታዎች በኤ 4 የወረቀት መጠን የሚዘጋጀውን ሳምንታዊ ሕትመት ሲጠቀሙ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ 24 ትምህርቶችን የያዘውንና በኤ 5 የወረቀት መጠን የተዘጋጀውን ጥራዝ ይጠቀማሉ። መምህሩ ወይንም ደግሞ የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ በኤ 4 የወረቀት መጠን ትምህርት ያድላል። ትምህርቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይንም ደግሞ በት/ቤት ይሞላል ወይንም ደግሞ ወደ ቤት ይወሰዳል። ከዚያም በተከታዩ ሳምንት ይመለሳል። በወሩ መጨረሻ መምህሩ ወይንም የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ ትምህርቶችን ይሰበስብና ያርማቸዋል። ነጥብም ይሰጣቸዋል። በተቻለ መጠንም ከእርማት በኋላ ለተማሪዎች መመለስ አለበት።

የተዘጋጁት ጥራዞች ጥቅም ላይ ከዋሉ በየሳምንቱ መጨረሻ እየተሰበሰቡ ይታረማሉ። በብዙ ምክንያቶች ይህ አስቸጋሪ እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህም በክፍል ውስጥ ጥራዞቹ ለተማሪዎች ይከፋፈላሉ። በዚህ ጊዜ መምህሩ/መሪው ከተማሪዎች ጋር አብሮ ይሰራል። ተማሪዎችም የጓደኞቻቸውን ስራዎች ያርማሉ፣ ነጥብም ይሰጣሉ። ከጥራዞቹ በስተጀርባ ለእያንዳንዱ ነጥብ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ እንዲሁም ተማሪው ስላሳየው እድገት አስተያየት መስጫ ቦታ አለ። እንዲሁም ከጥራዙ በስተመጨረሻ ሰርተፊኬት ተያይዟል። ይህ ሰርተፊኬት በቀላሉ ከጥራዙ ላይ ሊገነጠል የሚችል ሲሆን ተማሪው ባለፉት 6 ወራት ከሙቶ ያገኛቸውን ውጤቶች ይይዛል።

## ለመምህራን የተደረገ ዝግጅት

*መምህራን በራሳቸው ዘዴ ወይንም መንገድ፣ ተነሳሽነትና ሀሳብ ላይ የተመሠረተ አንዳችም ነገር እንዲያደርጉ አንጠብቅም። ለእንደዚህ አይነት ጉዳይ ምንም ቦታ አንሰጥም። የሚከተሉት ሀሳቦች የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ሀሳቦች ናቸው።*

- ***ከታሪኩ ጋር በሚገባ ራስን ማስተዋወቅ -*** *ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና በተጓዳኝ አብረውት ከሚሄዱት የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር በተቻለ መጠን ራሳቸውን ማስተዋወቅ አለባቸው። መምህሩ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከማስተማሩ በፊት ራሱ አጥንቶ ቢያጠናቅቅ ተመራጭ ነው። ለእያንዳንዱ ትምህርት የተዘጋጁት መምሪያዎችም በእቅድ ወቅት ስለ ሚረዱ በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል።*
- ***ትምህርቶችን በሚገባ መረዳት -*** *ከእያንዳንዱ የትምህርት እቅድ በላይ **"በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።"** የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። እነኝህም መምህሩ ገለፃውን ካጠናቀቀ በኋላና ተማሪዎችም ያንን የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚጨብጧቸውን ሁለት አላማዎች የያዙ ናቸው። የመጀመሪያው አላማ ከታሪኩ ስለ ቀሰሙት እውቀት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ስላገኙት እውቀት እንዲያሰላስሉና በተቻለ መጠንም ምላሽ እንዲሰጡና ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት ያበረታታል። እነኝህ የመማር አላማዎች በተሰጠው ትምህርት ውስጥ ያለውን ዋና ፅነስ ሀሳብ/እውነት የያዙ ናቸው። መምህራንም ራሳቸውን እንዲሁም የመማር የማስተማር ሂደቱን ለመገምገም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።*
- ***አስተዋውቁት/መግቢያ -*** *ሁሉንም ትምህርቶች የምንጀምረው ከራሳቸው ከተማሪዎች ልምምድና ካሉበት ሁኔታ በመነሳት ነው። ታሪኮችን በመግቢያው ውስጥ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን አቅርበናል። በዚህም ልጆች በትምህርቱ ማስጀመሪያ ነጥብ ላይ በመስተጋብር የተሞላ ውይይት እንዲያካሂዱ እናስችላቸዋለን።*
- ***የማስተማር ጊዜ -*** *የታሪኩን ቁልፍ ነጥቦች አቅርበናል። መምህራን ታሪኮቹን በሚያስተምሩበት ወቅት እነኝህን ቁልፍ ነጥቦች እንደማያነሷቸው ተስፋ እናደርጋለን። ሆኖም በሚያስምሩበት ወቅት ራሳቸውን ከታሪኩ ጋር በሚገባ አስተዋውቀው ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተማር ይጠቀሙባቸዋል። መምህሩ በትምህርቱ ውስጥ ያለውን ታሪክ ተማሪዎቹ በሚገባ እንዲረዱ ማድረግ አለበት። እንዲሁም ልጆቹ ታሪኩን ከተገነዘቡት በኋላ መስጠት ስላለባቸው ምላሽ አቅጣጫ ይጠቁማቸዋል። ከእያንዳንዱ ትረካ ጋር አብሮ የሚሄዱ ማብራሪያዎችንም አብረን ማቅረቡ ተገቢ ስለሆነ ይህንኑ አድርገናል። እነኝህም በኢታሊክስ (ITALICS) ተፅፈው ቀርበዋል።*
- ***የመማር ጊዜ -*** *ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር አብሮ የተያያዘ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለ። አንዳንድ ጊዜም ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተያይዘዋል። ምክንያቱም ተጨማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተማሪዎች በቀላሉ መማር እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ልጆች እነኝህን ቁልፍ ጥቅሶች እንዲማሩ እንዲሁም በተደጋጋሚ እንዲያስታውሱት እንደሚደረግ ተስፋ እናደርጋለን። ይህም ልጆች የቁልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እውቀት ግንባታ ማድረግ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል።*
- ***ማጠናቀቅ -*** *በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ሰርቶ ማሳያ/የመለማመጃ ጥያቄዎችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋቸውን የችሎታ ልክና መምህሩ በዚህ ረገድ ለተማሪዎቹ ሊያደርግላቸው የሚችለውን የእገዛ መጠን በተመለከተ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል። አንዳንዶች መምህሩ ታሪኩን ካነበበላቸውና ከታሪኩ ጋር በሚገባ ከተዋወቁ በኋላ ወደ ስራ ይገባሉ። ሌሎች ልጆች ደግሞ ታሪኩን ራሳቸው ማንበብ ይችላሉ። በሁለቱም መንገዶች ዋናው ሀሳብ ጥያቄዎቹን ለመስራት በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የልጆቹ አትኩሮት እንዲያርፍ ማድረግ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከት/ቤት ውጪ በሌሎች ቦታዎች የምትጠቀሙ ከሆነ ተማሪዎቻችሁን ባሉበት ቦታ በአካል ተገኝታችሁ መርዳት መቻል አለባችሁ። አለበለዚያ ተማሪዎቻችሁ ትምህርቱን እንደፈተና ወይንም ደግሞ የግድ መጠናቀቅ እንደላበት ስራ አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ። አስደሳች መሆን አለበት። ለዚህም ተማሪዎች እየሰሩ ባለበት ወቅት ማበረታታት አስፈላጊ ነው።*

- **የክለሳ ጊዜ -** በተቻለ መጠን ተማሪዎች በምን ያህል መጠን ትምህርቱን አውቀውታል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱንን አጫጭር ሙከራዎችን መስጠት ወይንም አስፈላጊ መሆኑን እንመክራለን። ይህም ትምህርቱን ለመከለስና የተማሪዎችን የመማር ፍጥነት ለማገዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።
- **ማሳየት -** በአንዳንድ ሁኔታዎች የቪዡዋል (የእይታ) ትምህርት መርጃዎች በቀላሉ ላይገኙ ቢችሉም በተቻለ መጠን ለሚታዩ ስዕሎች ወይንም ደግሞ ለሌሎች ቁሳቁሶች ትኩረት መስጠትና በተግባር ማዋል ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል። በትረካ ወቅት የእይታ ትምህርት መርጃዎች ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ። አስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችን በተመለከተ መረጃ ከተፈለገ ከሚከተለው ዌብ ሳይት ማግኘትና ስዕሎችንም ማውረድ ይቻላል። [www.freebibleimages.org (FBI)] ሌላው የእይታ መርጃዎችን የምናገኝበት ምንጭም Eikon Bible Art [info@eikonbibleart.com] ዌብ ሳይት ነው። ሆኖም ከዚህ ዌብ ሳይት የምናገኛቸው ምንጮች በሽያጭ የሚገኙ ናቸው። የፎቶ ኮፒ ማሽን ባለበት አንዳንድ ስእሎች ሊተልቁ ቀለም ሊቀቡና በትምህርት ወቅት ጥቅም ላይ ማዋል ሊውሉ ይችላሉ።

## ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የማስተማር ጊዜ

1) ጥቅሱ በወረቀት ወይንም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሊፃፍ ይችላል። ይህም የተለያዩ ቃላትን በማጉደል የሚደረግ ነው። ይህም ሁሉም የጥቅሱ ቃላት በሙሉ እስኪነሱና ተማሪዎችም ጥቅሱን በቃላቸው መድገም እስኪችሉ ድረስ ነው።
2) ቁልፍ ጥቅሱን ለማስተዋወቅ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ።
   ሀ) በሁለት ቡድኖች መስራት (በገመድ የመስቀል ዘዴ) - የቁልፍ ጥቅሱ የተለያዩ ፊደላት ተቀንሰው በምትካቸው ክፍት ቦታዎች አሉ። ልጆችም የትኞቹን ቃላት ቢጠቀሙ ጥቅሱን ማሟላት እስከሚችሉ ድረስ ይሰራሉ። ይህም ከመካከላቸው አንደኛው ልጅ ጥቅሱን እስከሚለየው ድረስ ይቀጥላል።
   ለ) ጥቅሱን ቀድሞ መፈለግ። መጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ የሚገኝ ከሆነ ተማሪዎች ቁልፍ ጥቅሱን ይፈልጋሉ። መጀመሪያ ጥቅሱን ያገኘው ልጅ አሸናፊ ይሆናል።

## ጊዜን ማቀድ

- **ቅደም ተከተል.** ለሁሉም የማስተማሪያ መምሪያዎች ተመሳሳይ ቅደም ተከተል እንጠቀማለን። ሆኖም ይህን ቅደም ተከተል መምህራን እንደአስፈላጊነቱ ሊቀያይሩት ይችላሉ።
  1. መግቢያና ትረካ - በግምት 15 ደቂቃ
  2. ቁልፍ ጥቅሱን የማስተማር ጊዜ - ከ5 እስከ10 ደቂቃ
  3. ስርቶ ማሳያውን ማጠናቀቅ - 20 ደቂቃ
  4. መልመጃና ሌሎች ስራዎች 5-10 ደቂቃ

ይህን አባባል ሁሌም አስታውሱት።

“የነገራችሁኝን እረሳለሁ።
የምታሳዩኝን አስታውሳለሁ።
አብሬያችሁ ስሰራ በሚገባ እረዳለሁ።”

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሲለበስ

| | ደረጃ 0 (ቅድመ መደበኛ ትምህርት)<br>ደረጃ 1 (ከ5-7 ዓመት)<br>ደረጃ 2 (ከ8-10 ዓመት) | ደረጃ 3 (ከ11-13 ዓመት) | ደረጃ 4 (14 ዓመትና ከዚያ በላይ) |
|---|---|---|---|
| የጀማሪዎች ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. U1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. U2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. U2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. U1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. U2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. U2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. U1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. U2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. U2 - የሉቃስ ወንጌል |
| ሀ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. ፀሎት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረትና ውድቀት<br>2. ዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ክንዋኔዎች<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. የክርስቲያን ሕይወት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ለ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የክርስቶስ የቀደመው ሕይወቱ<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. ምሳሌዎች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ፀሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ያዕቆብና ቤተሰቡ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የሐዋርያት ስራ 2፡42 ከፊት ለፊት ያለው መንገድ<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሕግ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ሐ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ዳንኤል<br>2. ተጨማሪ ተአምራት<br>3. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሳሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ዮናስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>3. ተጨማሪ ተአምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. እግዚአብሔር የተጠቀማባቸው የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. የኢየሱስ አባባሎች<br>3. የጌታ ኃይል<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ተጨማሪ የብሉይ ኪዳን ባሕርያት<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |

## ለ1 ታሪክ 1

**ማርያምና ዮሴፍ በቤተ-መቅደስ ውስጥ- ይህ ታሪክ እግዚአብሔርን ስለ ልጁ "አመሰግንሃለው" ስለ ማለት ነው።**

| | |
|---|---|
| | ***የምንማረው:*** <br>• ኢየሱስ የተወለደው የእግዚአብሔር ማዳን ለመሆን ነው። <br>• እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ልጁን ኢየሱስን ስለሰጠን ልናመሰግነው ይገባል። <br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 2:30*** <br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 2:22-38*** |
| ***መግቢያ*** | ስጦታን ስለመቀበል አውሩ ፤ ።አመሰግናለው። የሚለውን በምሳሌ ለማሳየት እንዲቀላችሁም የምትሰጡት አንድ ሁለት ስጦታ ብትይዙ ጥሩ ነው። ሲሰጣቸው በጣም ያስደሰታቸውን ስጦታ እንዲናገሩ ለህጻናት እድል ስጡ። ምንም ትንሽ ቢሆንም እንኳን ለማንኛውም ስጦታ ግን "አመሰግናለሁ" ማለት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ተናገሩ። <br>በዛሬው ታሪክ እግዚአብሔር በሰጣቸው ተላቅ ስጦታ (ኢየሱስ ክርስቶስ) አመስጋኝ የሆኑ ሰዎችን እናያለን። |
| ***የማስተማር ጊዜ*** | • ይህ ቀን ለማርያም እና ለዮሴፍ ልዩ ቀን ነበር። እግዚአብሔርን ለማመስገን ህጻኑን ኢየሱስን ይዘው እየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ-መቅደስ የሄዱበት ቀን ነው። ***(ሉቃስ 2:22-24)*** <br>• በቤተ-መቅደሱ ሳሉ አንድ እድሜው የገፋ ስምኦን የሚባል ሰው መጣ። ይህ ሰው የእግዚአብሔርን አዳኝ የመላኩን እቅድ ያውቅ ነበር። እንደውም አስደናቂ ቃል ተገብቶለታል፤ ይህም ኢየሱስን በዓይኑ ሳያይ እንደማይሞት ነበር። ስምኦን በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ማርያምና ዮሴፍን ተገናኘ። ይህ ህጻን በመላው ዓለም ምን አይነት ለውጥን እንደሚያመጣና ልዩ ስጦታ እንደሆነ ስምኦን ያውቅ ነበር። *ስምኦን ህጻኑን ኢየሱስን ይዞ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን ምን እንደተሰማው ከመጽሐፍ ቅዱስ ተመልከቱ።* ***(ሉቃስ 2:25-35)*** <br>• በመቀጠልም ሃና የምትባል ተለቅ ያለች ሴት ማርያምና ዮሴፍን ከህጻኑ ኢየሱስ ጋር አገኘቻቸው። እሱዋም ስለ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቀረበች። ከዚህም በኋላ ላገኘችው ሰው ሁላ ስለ ኢየሱስ ትናገር ነበር። ***(ሉቃስ 2:36-38)*** *እኛም ልክ እንደ ሃና የኢየሱስን የምስራች ለሌሎች ማካፈል አለብን።* <br>• *ስንት ሰዎች ናቸው ቤተ-መቅደስ ውስጥ "አመሰግናለው" ያሉት? እኛ ምናውቀው አራት ነው(ስማቸውን በድጋሚ ተናገሩ) ነገር ግን ከዚህም በላይ ሊኖሩ ይችላሉ። ለእኛም ቢሆን እግዚአብሔር ስለሰጠን ስጦታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመስገናችን በጣም አስፈላጊ ነው። ስምኦን ሁሌም በሂወቱ የኢየሱስን መወለድ ተስፋ ያደርግ ነበር። እኛ ደግሞ ወደ ኋላ ተመልክተን ኢየሱስን ስለተወለደልንና ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ በመሞት አዳኝ ስለሆነን እናመሰግነዋለን። እግዚአብሔር የሰጠንን ስጦታ ከሌላ ስጦታ ጋር ሲወዳደር ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ማስተዋል እንዲችሉ ልጆቹን አበረታቱ። በተጨማሪም እያንዳንዳቸው በግል እግዚአብሔር ስለሰጠን ስጦታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ስላረገልን ነገር ሁሉ ሁሌም እንዲያመሰግኑ አሳስቡ።* <br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።** <br>**አሳዩ:** ስምኦን እና ሃና ህፃኑ ኢየሱስን ሲያገኙ |
| ***የመማር ጊዜ*** | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ሉቃስ 2:30*** አብራሩ <br>*እነዚህ ቃላት ከስምኦን የምስጋና ፀሎት የተወሰዱ መሆናቸውን አስረዱ። መዳን ማለት ጌታ ኢየሱስ ኃጢአታችንን ከእኛ ሲወስድ የምናገኘው ነው።* |
| ***የክለሳ ጊዜ*** | ትምህርቱን ለመከለስ ያክል ተማሪዎቹን ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው <br>• ቤተ መቅደሱ የት ነበር? <br>• ማርያምና ዮሴፍ ከኢየሱስ ጋር በዚያ የተገኙት ለምንድን ነበር? <br>• ወደ እነርሱ የመጣው ሽማግሌ ሰውዬ ማን ነበር? <br>• ለስምኦን የተሰጠው ተስፋ ምን ነበር? <br>• ስለ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ያመሰገነችው ባልቴት ማን ትባላለች? <br>• ሃና ህፃኑን ኢየሱስ ካየች በኋላ ምን አደረገች? <br>• ከስምኦን እና ከሃና ምሳሌ ምን እንማራለን? <br>• ስለ ስምኦን እና ስለ ሃና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ክፍል ላይ እናገኛለን? |

## ለ1 ታሪክ 2

**በናዝሬት ውስጥ ማደግ - ይህ ታሪክ ስለ ኢየሱስ አስተዳደግ ያወራል።**

**የምንማረው:**

- ህፃን እያለ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አሳይቷል።
- የኢየሱስ ታዛዥነት ምሳሌአችን መሆኑ አስፈላጊ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 2:40***

**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 2:39-52***

### መግቢያ

ስለ ጠፋቹበት ወይንም ከወላጆቻቹ ስለተለያቹበት አጋጣሚ አውሩ። መቼ እና እንዴት ነው የተፈጠረው? የወላጆቻችሁስ ስሜት እንዴት ነበር? በዚህ ሀሳብ ላይ አተኩሩ።ወይም ጠቃሚ ከሆነ ከቤት ርቃችሁ የሄዳችሁበትን አጋጣሚ እና የነበራችሁን ስሜት አውሩ። በዛሬው ታሪክ ላይ ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ይዘው ከቤታቸው ራቅ ወዳለ ቦታ ሄደው እንደነበር ተናገሩ።

### የማስተማር ጊዜ

- ኢየሱስ የፋሲካ በአልን ለማክበር ከወላጆቹ ጋር ወደ እየሩሳሌም ሄዶ ነበር። *(የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ላላቸው እድሚያቸው ከፍ ላሉ ልጆች ምን እንደሚያመለክት አገናኙላቸው) ሀገር ውስጥ ካሉ ቦታዎች ጋር እያወዳደራቹ (ከእየሩሳሌም እስከ ናዝሬት 113 ኪ.ሜ) ምን ያህል ርቀት እንደተጓዙ እና እንዴት በእግር እንደሄዱ አውሩ። ግርግሩ፣ ጓደኞቹ፣ ሀንፃዎቹ፣ አስተማሪዎች ስለ አባቱ ስለ እግዚአብሔር በሚወሩበት ቤተ-መቅደስ ውስጥ የመገኘት እድል እነዚህ ሁሉ ተደምረው 12 አመት እድሜ ለሆነው ኢየሱስ ምን ያህል አስደሳች አጋጣሚ ሊሆን እንደሚችል አብራሩ።* ***(ሉቃስ 2:42)***
- *ወደ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ ከመጀመሪያው ቀን በኋላ ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስ መጥፋቱን አስተዋሉ። ምን ሊሰማቸው እንደሚችል፣ እዛ ሁሉ ህዝብ መሀል እንዴት ሊፈልጉት እንደሚችሉና ወደ እየሩሳሌም ሊመለሱ እንደወሰኑ አስቡት።* ***(ሉቃስ 2:43-45)***
- ከሶስት ቀናት በኋላ ኢየሱስን በቤተ-መቅደስ ውስጥ ከአስተማሪዎች መሃል ቁጭ ብሎ አገኙት። *ከመግቢያው ጋር በማመሳሰል ኢየሱስን ሲያገኙት ምን አይነት እረፍት ሊሰማቸው እንደሚችል አስረዱ።* ኢየሱስ በሚሰማበት እና በሚጠየቅበት ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ይሄን ያህል በማወቁ አስተማሪዎቹ ተደነቁ። ማርያምና ዮሴፍም ተደንቀዋል። *የኢየሱስን እና የማርያምን ንግግር በመመልከት ኢየሱስ በልጅነቱ ጭምር በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የእርሱን ስራ እንደሚሰራ እናያለን። ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስ የሚያወራውን በሙሉ ለመረዳት ከብዷቸው ነበር።* ***(ሉቃስ 2:46-50)***
- ከዚ በኋላ ኢየሱስ ከማርያምና ከዮሴፍ ጋር ወደ ናዝሬት ተመለሰ። በሁሉም ነገር ለእነርሱና ለአባቱ ለእግዚአብሔርም ታዛዥ ነበር። *መጽሐፍ ቅዱስ ለወላጆቻችን ታዛዥ መሆን እንዳለብን ይነግረናል።* ***(ኤፌ 6:1)*** *ይህን በማድረግ የኢየሱስን ፈለግ እንከተላለን።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**

**አሳዩ:** የ12 አመቱ ልጅ ኢየሱስ በእየሩሳሌም

### የመማር ጊዜ

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ፤ ***ሉቃስ 2:40***

አብራሩ። ኢየሱስ በምን አይነት መንገዶች እንዳደገ አስርዱ። እኛም በእነዚህ መንገዶች ማደግ እንችላለን ከምንም በላይ እግዚአብሔርን የምንወደውና የምናገለግለው ሰዎች ሆነን እንድናድግ ይፈልጋል።

### የከለሳ ጊዜ

ቀጥሎ ያሉትን እውነት ወይም ሀሰት ዓረፍተ ነገሮች እንደ ፈተና ተጠቀሙት

- የፋሲካ በአል የተከበረው በእየሩሳሌም ነበር።
- በዚህ ተሪክ ውስጥ ኢየሱስ የ10 አመት ልጅ ነው።
- ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ያገኙት ከአንድ ቀን በኋላ ነበር።
- ኢየሱስ የዘመድ ቤት ውስጥ ነበር።
- ማርያም ለኢየሱስ ተጨንቀው እንደነበር ነገረችው።
- ኢየሱስ የአባቱን ስራ እየሰራ ነበር።
- እግዚአብሔር የኢየሱስ አባት ነው።
- ኢየሱስ ወደ ናዝሬት ተመልሶ ማርያምና ዮሴፍን ታዘዘ።

## ለ1 ታሪክ 3

**በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ መጠመቅ - ይህ ታሪክ ኢየሱስ በዮሐንስ ስለመጠመቁ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው**:<br>• የኢየሱስ ህይወት ከኃጢአት የነፃ እና ሁሌም አባቱን የሚያስደስት ነበር።<br>• እኛ ኃጢአተኞች በመሆናችን ንስሀ መግባት ይኖርብናል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: ***ሉቃስ 3:22***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**: ***ሉቃስ 3:1-22*** |
| *መግቢያ* | ህዝብ ስለሚሰበስቡ ሰዎች አውሩ ለምሳሌ :-ፕሬዝደንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ ነጋዴ፣ አዝናኝ ነገሮችን ሚያቀርቡ ሰዎች። ሁሉም ሰው ምን እየተፈጠረ እንዳለ ማየት እና ምን እየተባለ እንዳለ ለመስማት ይጓጓል። መጥምቁ ዮሐንስም ከዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ መስበክ ሲጀምር ከዚህ የተለየ ነገር አልተፈጠረም። ይህ በረሃ ውስጥ ይኖር የነበረ የተለየ ሰው ምን እንደሚል ለመስማት ህዝቡ ተሰበሰበ። ***(ማቴዎስ 3:4)*** |
| *የማስተማር ጊዜ* | • ዩሃንስ ነብይ ነበረ። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ አስፈላጊ መልዕክት ነበረው። ለሰዎቹ ኃጢአተኞች እንደሆኑ፣ በዚህም መፀፀት እንዳለባቸውና ሊመለሱ እንደሚገባ ይናገር ነበር። እነርሱም በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ይጠመቁ ነበር። ይህም ሰዎቹ የመለወጥ ፍላጎት እንደነበራቸው ያሳያል። ***(ሉቃስ 3:2፣3፣7)*** *ልጆቹ የክርስቲያን የጥምቀት ሥነ ስርዓት አይተው የሚያውቁ ከሆነ ከእነርሱ ጋር በማገናኘት አውሩ። ሁላችንም ለኃጢአታችን ንስሃ መግባት እንዳለብንም ተናገሩ።*<br>• ሰዎቹ ስለ ዮሐንስ ማንነት እርግጠኛ አልነበሩም። እግዚአብሔር ሊልከው ቃል የገባልን ሰው ይሆን? ዮሐንስ ከእርሱ በኋላ በጣም ኃይለኛና ከእርሱ የሚበልጥ እንደሚመጣ ተናግሯል። *ማን ሊሆን ይችላል?* ***(ሉቃስ 3: 15,16)***<br>• ከዕለታት አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ መጥቶ ከተቀሩት ሰዎች ጋር ተጠመቀ። *ኢየሱስ ከመጠመቁ በፊት ማድረግ የሌለበት ነገር ምን ነበር? ኢየሱስ ኃጢአት ስለሌለበት ከሁላችንም የተለየና ንስሀ መግባት እንደማያስፈልገው አብራሩ።* ነገር ግን ኢየሱስ እንደኛ ሰው መሆኑን ሊያሳይ ስለፈለገና እግዚአብሔር ያዘዘውን ለመፈፀም ሲል ተጠመቀ። ከኢየሱስ ጥምቀት በኋላ አስደናቂ ነገር ተፈጠረ። እግዚአብሔር ከሰማይ በኢየሱስ ደስ እንደሚለው ተናገረ። *በመቀጠልም መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወረደበት።* ***(ሉቃስ 3:21፣22)***<br>• *ኢየሱስ እንዳደረገው አድርገን እግዚአብሔርን ማስደሰት አንችልም። ነገር ግን በኃጢአታችን ከልባችን ተፀፅተን ንስሀ ስንገባና ለእርሱ መኖርን ስንመርጥ ይደሰትብናል።*<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ**: ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው |
| *የመማር ጊዜ* | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ሉቃስ 3:22*** አብራሩ። ልጆቹ ትምህርቱን እንተረዱ ለማረጋገጥ ቀላል ጥያቄዎችን ጠይቁ። |
| *የክለሳ ጊዜ* | ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ጠይቁ<br>• መጥምቁ ዮሐንስ የነበረው የት ነው?<br>• ዮሐንስ መልዕክቱን ከየት ነበር ያመጣው?<br>• ዮሐንስ ለሰዎቹ ንስሀ እንዲገቡ ይናገር ነበር። ንስሀ ምን ማለት ነው?<br>• ሰዎቹ ንስሀ ከገቡ በኋላ ዮሐንስ ምን ያረጋቸው ነበር?<br>• ከእርሱ በኋላ ሊመጣ ያለውን ዮሐንስ እንዴት ነው የገለፀው?<br>• ኢየሱስ የፈለገው ዮሐንስ ምን እንዲያደርግ ነበር?<br>• የኢየሱስ ጥምቀት ከሌሎቹ በምንድን ነው ሚለየው?<br>• ምን በማድረግ ነው እግዚአብሔርን የምናስደስተው? |

## ለ1 ታሪክ 4

## በበረሃ ውስጥ መፈተን - ይህ ታሪክ ትክክል ላልሆኑ ነገሮች እንቢ ስለማለት ነው

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው**:<br>• ጌታ ኢየሱስ ምንም ኃጢአት አላረገም።<br>• በፈተና ጊዜ እርሱ ሊረዳን ዝግጁ ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: ***ሉቃስ 4:8***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**: ***ሉቃስ 4:1-13*** |
| *መግቢያ* | ለልጆቹ ሊፈተኑ ሚችሉበትን አጋጣሚዎች እንደ ምሳሌ ስጡ (በደረጃ 2 ትምህርት ላይ መጀመሪያ አካበቢ ያሉትን ምሳሌዎች ተመልከቱ) በተግባር ደረጃ ፈተናን እንዴት ሊያስወግዱ እንደሚችሉ አውሩ። ዛሬ የምናየው ጌታ ኢየሱስ በተፈተነበት ጊዜ ምን አድርጎ እንደነበር ነው። |
| **የማስተማር ጊዜ** | • *ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወደ በረሃ መራው። በበረሃ ውስጥ ለ40 ቀን ያክል መቆየት ምን ሊመስል እንደሚችል አስረዱ። ሙቀቱ፣ አካባቢው ደረቅ ነው፣ በዛ ላይ ደግሞ ብቻውን ነው። እነዚህን ነገሮች አጠቃሉ። 40 ቀን ምን ያህል ረጅም መሆኑን ለማስረዳት ጥሩ የሆን ምሳሌ ተጠቀሙ።* ***(ሉቃስ 4:1)***<br>• *ምንም አይነት ምግብ ካለመብላቱ የተነሳ በጣም ተርቦ ነበር። ከሁሉም ነገር በላይ ምግብ ያስፈልገዋል። ሰይጣን ለኢየሱስ አቅርቦለት የነበረውን ጥያቄ ጥቀሱ። ምግብ ለማግኘቱ ይሄ በጣም ቀላል መንገድ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ሰይጣን ያቀረበውን ፈተና ስህተት እንደሆነ በማሳየት የእግዚአብሔርን ቃል ተጠቅሞ መልስ መለሰ።* ***(ሉቃስ 4:3-4)***<br>• *ለሁለተኛው ጊዜ መጥቶ ሰይጣን የአለምን ነገስታት ሁሉ ሊያይበት ወደሚችለው ታላቅ ተራራ ኢየሱስን ወሰደው። ኢየሱስ ቢሰግድለት ነገስታቱ ሁሉ የእርሱ እንደሚሆኑ ሰይጣን ነገረው። ኢየሱስ ግን እንዲህ ብሎ መለሰ ።ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ብቻ ስገድ ተብሎ ተፅፏል።። ኢየሱስ አሁንም የሰይጣን ሀሳብ የተሳሳተ መሆኑን ለማሳየት የተጠቀመው የእግዚአብሔርን ቃል ነበር።* ***(ሉቃስ 4:5-8)***<br>• *በመጨረሻም ሰይጣን ኢየሱስን እየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ-መቅደስ የላይኛው ጫፍ ላይ አወጣው። ኢየሱስ የእውነትም የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ ራሱን ከዚህ ከፍታ ላይ ቢወረውር ምንም እንደማይሆን ነገረው። ኢየሱስ ኃይሉን እንዲገልጥ ሰይጣን እየፈተነው ነበር። ኢየሱስ ግን ይህ ስህተት እንደሆነ ስለሚያውቅ በድጋሚ ከእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም መለሰለት። በዚህ ሰዓት ሰይጣን ኢየሱስን ትቶት ሄደ።* ***(ሉቃስ 4: 9-13)*** *ሰይጣን ለምን የሄደ ይመስላችኋል?ተሳክቶለት ነበር እንዴ?ኢየሱስስ እንዴት ነው ፈተናውን ያሸነፈው?*<br>• *ኢየሱስ ምንም ኃጢአት እንዳላደረገ በመናገር አጠቃሉ። ከሰይጣን ይልቅ በጣም ኃይለኛ ነው።አባቱን እግዚአብሔርን እየታዘዘ እንደነበረ ሰይጣንን ለማሳየት የእግዚአብሔርን ቃል ተጠቅሟል።እኛ የኢየሱስ ከሆንን ትክክል ላልሆኑ ነገሮች እንቢ እንድንል አቅምን ይሰጠናል። ልክ እንደ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል የምናውቅ ከሆነ ትክክል የሆነውን ነገር እንድናደርግ አቅምን ይሰጠናል።*<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ**: ስዕል፡- ኢየሱስ በበረሃ ውስጥ ተፈትኗል። |
| **የመማር ጊዜ** | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ሉቃስ 4: 8*** አብራሩ። ልጆቹ የዚህን ክፍል አውድ እንደተረዱት አረጋግጡ። ማነው የተናገረው? ለማን ነው የተነገረው? ለምንድን ነው ኢየሱስ እነዚህን ቃላት የተጠቀመው? |
| **የክለሳ ጊዜ** | ከፈተና ይልቅ ልጆቹ እስካሁን የተማሩትን የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ማስታወስ የተሻለ ነው።ለምሳሌ የእያንዳንዱን ቀን ትምህርት ዋና ሀሳብ በአጭሩ በመፃፍ፣ተለቅ ያሉ ልጆች ከሆኑ በቡድን ሆነው ለአስተማሪው እንዲያቀርቡ ማድረግ . |

## ለ2 ታሪክ 1
**ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ቀየረ - ይህ ታሪክ ኢየሱስ በአንድ ሰርግ ላይ ስለ መገኘቱ ነው።**

**የምንማረው:**
- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ይህን የመጀመሪያውን ተዓምራት አደረገ።
- ልክ ታሪኩ ላይ እንዳሉት ባሪያዎች ኢየሱስን ልንታዘዘው ይገባል።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 2: 5***
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዮሐንስ 2: 1-11***

### *መግቢያ*

በእናንተ ባህል ሰርግ ላይ ምን ምን እንደሚከናወን አውሩ።ተማሪዎችም በዚህ ላይ ያላቸውን ሀሳብ እንዲናገሩ እድል ስጧቸው።የሚቻል ከሆነ ፎቶ ብትይዙ ጥሩ ነው። ሰርጉ ላይ እንደታቀደው ያልታሰበ ነገር ቢፈጠርስ? አንድ ሁለት ምሳሌዎችን ስጡ።
በዛሬው ታሪክ ላይ ጌታ ኢየሱስ፣ደቀመዛሙርቱአ እና እናቱ ማርያም በቃና በተደረገ አንድ ሰርግ ላይ እንግዶች ነበሩ። ***(ዮሐንስ 2: 1-2)*** ምን እንደተፈጠረ እንመልከት።

### *የማስተማር ጊዜ*

- *የሰርጉ ሁኔታ አስረዱ። ደስተኞቹ ሙሽሪት እና ሙሽራ፣ እንግዶቹ፣ ወሬ እና ሳቅ፣ ጣፋጭ ምግብና መጠጥ፣ ሁሉም በሰርጉ እየተደሰተ። ነገር ግን ማርያም የሆነ ችግር እንደነበረ ተረዳች። ምንም አይነት ወይን አልነበረም። ሁሉም አልቋል። በዚህ ሰአት ሙሽሪት እና ሙሽራ ምን ሊሰማቸው ይችላል? ማርያም ምን ማድረግ እንደነበረባት ታውቃለች። ቀጥታ ሄዳ ለኢየሱስ ተናገረች። ለኢየሱስ ማንኛውንም አይነት ችግራችንን ልንነግረው ምንችለው አንደኛ መፍትሄያችን እንደሆነ አስረዱ። ወደ እርሱ ልንፀልይ እንችላለን። በመቀጠልም ማርየም ወደ ሰራተኞቹ ዞራ "እርሱ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" አለቻቸው። ኢየሱስ ሊረዳቸው እንደሚችል ማርያም ታውቅ ነበር። በእርሱ ሙሉ እምነት ነበራት።* ***(ዮሐንስ 2: 3-4)***
- *በክፍሉ ውስጥ ስድስት ትላልቅ (ወደ 1ሜትር የሚጠጉ) የድንጋይ እንስራዎች ነበሩ። እንስራዎቹ ለምግብ መስሪያነት ወይንም ሰዎች ለሚታጠቡበት የሚሆን ውኃ ማስቀመጫዎች ናቸው። እንስራዎቹን በውኃ እስከ አፋቸው እንዲሞሏቸውና ትንሽ በመቀጠልም ቀድተው የሰርጉ ሀላፊ ወደ ሆነው ሰው እንዲወስዱት ኢየሱስ ሰራተኞቹን አዘዘ። ይሄ ለማድረግ አዲስ የሆነ ነገር ነበር። ምክንያቱም በእርግጠኝነት ውኃ ነበር። ያስደነቃቸው ነገር ያላቸውን ካደረጉ በኋላ ውኃው ወደ ወይን ተቀይሯል። ሁሉም የተስማሙበት ነገር ቢኖር ወይኑ በፊት ከነበረው የሚበልጥና በጣም ምርጥ ወይን እንደሆነ ነው።* ***(ዮሐንስ 2: 6-10)*** ጌታ ኢየሱስ ሁሌም ምርጡን ነው የሚሰጠው።
- *ይሄ ተአምራት እንደሆነ አስረዱ። ኢየሱስ ያደረገውን ማንም ሊያደርገው አይችልም ነበር። ያደረገውም ሁሉንም ፈጣሪ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ሰለሆነ ነው።*
- *ሰራተኞቹ ለኢየሱስ መታዘዛቸው በጣም ጠቃሚ ነበር። ሰራተኞቹ በይታዘዙት ኖሮ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ተማሪዎችን ጠይቁ። እኛ ጋር ያለው ችግር ኃጢአታችን መሆኑን አውሩ። ኢየሱስ ለችግራችን መፍትሄ አለው ምክንያቱም በመስቀል ላይ የሞተው የኃጢአታችንን ቅጣት ለመቀበል ነው። ነገር ግን ሙሉ እምነታችንን በእርሱ ላይ ስናደርግ ብቻ ነው ኃጢአታችንን ይቅር የሚለውና በህይወታችን ተአምራትን ሚያደርገው።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**
**አሳዩ:** ስዕል፡- ኢየሱስ በሰርግ ላይ

### *የመማር ጊዜ*

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ዮሐንስ 2: 5*** አብራሩ። የታሪኩን አውድ ተናገሩ። ልጆቹ ‹‹እሱ›› የሚለው ማንን እንደሚያመለክት ማወቃቸውን አረጋግጡ።

### *የክለሳ ጊዜ*

ታሪኩን ለመከለስ ያክል ተማሪዎችን ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው:
- ሰርጉ የተካሄደው የት ነበር?
- በሰርጉ ላይ የተገኙትን የአንዳንድ እንግዶች ስም ጥቀሱ?
- ሰራተኞቹ ኢየሱስን እንዲሰሙት የነገራቸው ማነው?
- ኢየሱስ ሰራተኞቹን ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው?
- ምን ያህል የውኃ እንስራዎች ነበሩ?
- ሰራተኞቹ ከእንስራው ውስጥ ሲቀዱ ምንድን ነው የተፈጠረው?
- ሁሉም የተስማማው በምንድን ነው?
- ኢየሱስ ይህን ተአምራት ለምን ማድረግ ቻለ?
- በእኛ ህይወት ያለው ችግር ምንድን ነው?
- ከሰራተኞቹ ምን እንማራለን?

## ለ2 ታሪክ 2

**ኢየሱስ የታመመውን ልጅ ፈወሰ - ይህ ታሪክ ስለ ኢየሱስ ኃይል ነው።**

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው:**<br>• ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ የመፈወስ ኃይል ነበረው።<br>• ኢየሱስን ልክ የንጉስ ቤቱ ሹም እንዳመነው እኛም እንድናምነው ይፈልጋል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 4: 50***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዮሐንስ 4: 46-54*** |
| **መግቢያ** | ያለፈውን ሳምንት ታሪክ ከልሱ። ሰርጉ ላይ ምን ተፈጠረ?የት ነው የነበረው? የተአምራቱ ዜና እንዴት በቃና እና ከዚያም ባሻገር እንደተዳረሰ አውሩ። |
| **የማስተማር ጊዜ** | • ከትንሽ ጊዜ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ወደ ቃና ተመለሰ። በአቅራቢያ ከሚገኝ ከተማ ከቅፍረናሆም አንድ የንጉስ ቤት ሹም የሆነ ሰው ኢየሱስ በቃና እንደነበረ ሰማ። ልጁ በጣም ታሞበት ነበር ። ሹሙ ኢየሱስ ቤቴ ቢመጣ ልጄን ይፈውስልኛል ብሎ አሰበ። ***(ዮሐንስ 4: 47)*** ለደረጃ ሁለት ተማሪዎች ሁለቱን ከተማዎች የሚያሳይ ካርታ መጠቀም ትችላላችሁ።<br>• ሹሙ ኢየሱስን ***ለማግኘት 32.2*** ኪሎ ሜትር ሚየክል ተጉዞ ነው የመጣው። አስቡት ምን ሊሰማው እንደሚችል - ድካም ጭንቀት … አብሮት እንዲመለስ ኢየሱስን ለመነው። ስለ ልጁ ለኢየሱስ ነገረው። ኢየሱስም ወደ ቤቱ እንዲመለስና ልጁንም በህይወት እንደሚያገኘው ተናገረ። ኢየሱስ አብሮት ሊመለስ አልነበረም። በዚህ ሰአት ሹሙ ምን ሊል እንደሚችል አውሩ እና የኢየሱስን ቃል መቀበሉንም አብራሩ። በኢየሱስ ላይ ጠንካራ እምነት ስለነበረው ኢየሱስ ልጁን ለመፈወስ ይሄን ያህል ርቀት መጓዝ እንደሌለበት ያውቅ ነበር። ***(ዮሐንስ 4: 47-50)*** ኢየሱስ ከእኛ ሚፈልገው ይሄን አይነት እምነት እንደሆነ አብራሩ። ልናየው አንችልም ድምፅ አውጥቶ ሲያወራም ላንሰማ እንችላለን ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በቃሉ ቃል ገብቶልናል እንደሚወደን እና ይቅር ሊለንም እንደሚፈልግ ተናግሯል።<br>• ሹሙ ወደ ቤቱ በመሄድ ላይ ሳለ ሰራተኞቹ ጥሩ ዜና ይዘው ተገናኙት። ምን እንደሆነ እንዲገምቱ ለተማሪዎች እድል ስጡ። እውነትም ልጁ ተፈውሷል። መቼ እንደተሻለው ሰራተኞቹን ሲጠይቅ ልክ ኢየሱስ ልጅህ በህይወት ይኖራል ባለበት ሰአት እንደሆነ ተገነዘበ። ሙሉ ቤተሰቡ በጣም ተደሰተ። ኢየሱስ እንደሚለው የእውነትም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሁሉም እርግጠኛ ነበሩ። ***(ዮሐንስ 4: 51-53)***<br>• እኛም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ልናምን ይገባል። በእርሱ ላይ ያለንን እምነት እንድናሳየው ይፈልጋል። በዚህ እኛም የእውነት ደስተኞች እንሆናለን።<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:** መልካም ዜና ሲነግት:- |
| **የመማር ጊዜ** | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ዮሐንስ 4: 50*** አብራሩ። የአንድን ሰው "ቃል" በመውሰድ ሙሉ ለሙሉ ማመን ምን ማለት እንደሆነ አጠናክራችሁ ግለጹ። |
| **የክለሳ ጊዜ** | ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:<br>• የሹሙ ችግር ምን ነበር?<br>• ኢየሱስን የት ነው ያገኘው?<br>• ምን ያህል ነበር የተጓዘው?<br>• ኢየሱስ ምን እንዲያደርግ አዘዘው?<br>• ሹሙ ወደ ቤቱ በመሄድ ላይ ሳለ ማንን ነው የገኘው?<br>• ምን ዜና ነበር ይዘው የመጡት?<br>• ልጁ መቼ ነበር የተሻለው?<br>• የጎደለውን ቃል ሙሉ ። የንጉስ ቤቱ ሹም ኢየሱስን በሙሉ ልቡ __________ ። |

<u>ለ2 ታሪክ 3</u>

**ኢየሱስ እና በርጠሜዎስ - ይህ ታሪክ ስለ አንድ አይነስውር ሰው መብራት እና ቀጥሎም ኢየሱስን ስለመከተሉ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው:**<br>• ጌታ ኢየሱስ በርጠሜዎስን ሊረዳው ፈለገ ህይወቱንም የመቀየር ኃይል ነበረው።<br>• ኢየሱስ ኃጢአታችንን ከእኛ ሊወስድ እና ህይወታችንን ሊለውጥ ይፈልጋል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማርቆስ 10: 52***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ማርቆስ 10: 46-52*** |
| *መግቢያ* | ማየት አስገራሚ ስጦታ መሆኑን አውሩ-የተለያዩ ቀለማትን ማየት መቻል፣ ቦታዎችን ማድነቅ፣ ሰዎችን መለየት፣ መጽሐፍ ማንበብ፣ ጨዋታ መጫወት፣ ቴሌቪዥን ማየት እና የመሳሰሉትን። በጥንቃቄ በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ አይነ ስውር ሆኖ መኖር እንዴት ሊሆን እንደሚችል አስረዱ። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ለአይነስውር ሰው ህይወት ምን ያህል ከባድ ሊሆን እንደሚችል አስረዱ። |
| የማስተማር ጊዜ | • በርጠሜዎስ በኢያሪኮ ይኖር የነበረ አይነስውር ሰው ነው። ለእርሱ ሁሉም ቀናቶች አንድ አይነት ነበሩ-በህይወት ለመኖር ሲል ከመንገድ ዳር ይለምናል። ነገር ግን ዛሬ የተለየ ቀን ነው። የነበረውን ጫጫታ ፣ ሁከት እና ኢየሱስ ሊመጣ እንደሆነ በርጠሜዎስ ሲሰማ ምን እንደሆነ አስረዱ። በርጠሜዎስ ይህን ሲሰማ በጣም ጓጉቶ ነበር። ኢየሱስ ከዚህ በፊት ያደረጋቸውን ነገሮች ሰምቷል። ኢየሱስ ምን እንዲያደርግለት የፈለገ ይመስላችኋል? በርጠሜዎስ ኢየሱስ ሊረዳው እስከሚችለው ድረስ መጮህ ጀመረ። አንዳንድ ሰዎች ተናደውበት ዝም እንዲል ቢጠይቁትም እንኳን እሱ ግን ደምፁን ከፍ አድርጎ መጮሁን ቀጠለ። ***(ማርቆስ 10: 46-48)*** ኢየሱስ ብቻ ነበር ዓይኑን ሊያበራለት የሚችለው ስለዚህም በርጠሜዎስ ያደረገው ነገር ትክክል እንደሆነ አስረዱ። የእኛን ኃጢአት ይቅር ሊልልን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ልክ በርጠሜዎስ ኢየሱስን ማግኘት እንደነበረበት ሁሉ እኛም ከእርሱ ጋር ጊዜ ያስፈልገናል።<br>• በዚያ ሰዓት ኢየሱስ መሄዱን አቁሞ በርጠሜዎስን ወደ እርሱ እንዲጠሩት አዘዛቸው። እንዴት ምላሽ እንደሰጠ አስረዱ። በርጠሜዎስ አሁን ምን ሊሰማው ይችላል? ኢየሱስ ምን እንደሚፈልግ ጠየቀው እርሱም ማየት እንደሚፈልግ ተናገረ። ኢየሱስም እምነቱ እንደፈወሰው እና መሄድ እንደሚችል ነገረው። በዚያ ሰዓት በርጠሜዎስ ማየት ቻለ! በርጠሜዎስ በዙሪያው ምን ሊያይ እንደሚችል ተማሪዎች እንዲገምቱ እድል ስጡ። ኢየሱስን በመንገድ ላይ በመከተሉ ምን እንደተሰማውና ያለውንም ምላሽ አብራሩ። ***(ማርቆስ 10: 49-52)***<br>• በርጠሜዎስ ኢየሱስን ያገኘበትን ቀን መቼም ቢሆን አይረሳውም።ኢየሱስ ተአምራትን አድርጎለታል ህይወቱም ተቀይሯል። ጌታ ኢየሱስ ውስጣችንን በመለወጥና ኃጢአታችንን በማስወገድ የበለጠ ተአምራትን በህይወታችን ሊያደርግ ይፈልጋል።ወደ እርሱ ስንመጣ እና በእርሱ ስንታመን ልክ እንደ በርጠሜዎስ እውነተኛ ደስታ ይኖረናል።<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:** ስዕል፦ ኢየሱስ አይነስውሩን ሰው ፈወሰ። |
| የመማር ጊዜ | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ማርቆስ 10: 52*** አብራሩ። የበርጠሜዎስ "እምነት" በኢየሱስ ላይ የነበረው መታመን እንደሆነ አስረዱ። ኢየሱስ በእርሱ ላይ እምነት እንዲኖረን ይፈልጋል። |
| የክለሳ ጊዜ | ቀጥሎ ያሉትን እውነት ወይም ሀሰት ዓረፍተ ነገሮች ተጠቀሟቸው:<br>• በርጠሜዎስ ቢቃና ነበረ።<br>• አይነስውር ነበረ።<br>• ማውራት አይችልም ነበረ።<br>• ኢየሱስን የሚያዩ ብዙ ሰዎች ነበሩ።<br>• ሰዎች ዝም እንዲል ከነገሩት በኋላ በርጠሜዎስ ፀጥ ብሎ ነበር።<br>• ኢየሱስ የበርጠሜዎስን ድምፅ ላለመስማት እየሞከረ ነበር።<br>• በርጠሜዎስ ተነስቶ ወደ ኢየሱስ መጥቶ ነበር።<br>• ወደ ኢየሱስ እንዳይመጣ ግርግሩ ይዞት ነበር።<br>• በርጠሜዎስ ኢየሱስን ከተገናኘ በኋላ መለመኑን ቀጥሎ ነበር።<br>• ጌታ ኢየሱስ ለእያንዳንዳችን ተአምራትን ሊያደርግ ይችላል። |

# <u>ለ2 ታሪክ 4</u>

## ኢየሱስ ለምፃሞቹን ሰዎች ፈወሰ - ይህ ታረክ ኢየሱስን “አመሰግንሃለው” ስለ ማለት ነው።

<table>
<tr><td></td><td>

**የምንማረው:**

- ለምፃሞቹ ሰዎች ኢየሱስን ታዘው ተፈወሱ።
- ጌታ ኢየሱስ ስለ መልካምነቱ እንድናመሰግነው ይፈልጋል።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***መዝሙር 107: 21***<br>
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 17: 11-19***

</td></tr>
<tr><td>መግቢያ</td><td>

አመስጋኝ ስለ መሆን አውሩ። በየቀኑ ሊያመሰግኑ የሚችሉባቸውን ምክንያቶችን (ምግብ፣ ውኃ፣ ቤት፣ ጤና፣ ቤተሰብ፣ ት/ቤት) ልጆቹን ጠይቁና እንደ ዝርዝር ፃፏቸው። እግዚአብሔር የሚየስደስቱንን መልካም ነገሮች ሁሉ ሰጪ እንደሆነ አስረዱ። ይህንን እድል ያላገኙትን በማሰብ በምስጋና ፀሎት ጀምሩ።

</td></tr>
<tr><td>የማስተማር ጊዜ</td><td>

- የዛሬው ታሪክ ከባድ ህይወት ስለነበራቸው 10 ሰዎች ነው። *ለምፅ እንዴት ተፅእኖ እንዳሳደረባቸው አስረዱ።*
- አንድ ቀን ግን ኢየሱስ በሚኖሩበት አካባቢ የተለየ ነገር ተፈጠረ። ከሰው ጋር መገናኘት ባይችሉ እንኳን ኢየሱስን በርቀት እያዩ ሊረዳቸው እንደሚችል ያስቡ ነበር። በአንድ ላይ የሚችሉትን ያክል ጮክ ብለው “ጌታ ኢየሱስ ሆይ ምህረትን አድርግልን!”እያሉ ጠሩት። ***(ሉቃስ 17: 11-13)***
- ኢየሱስም ሰምቶ መልስ ሰጣቸው። ሂዱና ራሳችሁን ለካህን አሳዩ አላቸው። *በህጉ መሰረት አንድ ሰው ከለምፁ ከነፃ ራሱን ለካህን ሊያሳይ እንደሚገባ አብራሩ።* እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ይፈውሰናል ብለው ስላሰቡ ወዲያውኑ ታዘው ሄዱ። በመንገድ ላይም ሳሉ በድንገት ለምፃቸው ጠፋ! ኢየሱስ ፈውሷቸዋል። *ምን ተሰምቷቸው ይሆን?* ***(ሉቃስ 17: 14)*** *ጌታ ኢየሱስን በመታዘዛቸው ትክክለኛ ነገር ነው ያደረጉት። እርሱ ለእኛ ያዘጋጀውን በረከት ወይም መልካም ነገሮች እንድናገኝ በእርሱ ልናምን እና ልንታዘዘው ይገባል።*
- አስሩ ሰዎች በተፈጠረው ለውጥ በጣም ተገርመወል ነገር ግን “አመሰግናለው” ለማለት ያሰበው አንዱ ብቻ ነበር። ስለሆነው ነገር እግዚአብሔርን እያመሰገነ በፍጥነት ወደ ኋላ ተመልሶ ኢየሱስን አገኘና እግሩ ስር ወደቀ። *ይህ ሰው ሳምራዊ እንደነበረና ከኢየሱስ ወይንም ከሌሎቹ ሰዎች ከተለየ ሀገር እንደመጣ አብራሩ።* ኢየሱስ በዚህ ሰው ምስጋና እና በመታዘዙ ባሳየው እምነት በተለየ መልኩ ተደስቶበታል። *ኢየሱስ ስለ ሌሎቹ ዘጠኙ ሰዎች ምን የሚሰማው ይመስላችኋል?* ***(ሉቃስ 17: 15 -19)*** *በዚያ ቀን በጣም ደስተኛ የነበረው ሰው ማን ይመስላችኋል?*
- *እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል (በዝርዝር ስለ ፃፏቸው ነገሮች ተማሪዎችን አስታውሱ) በተጨማሪም ኢየሱስ ህይወቱን ስለሰጠን እና ኃጢአታችንን ይቅር ስላለን ልናመሰግነው ይገባል። ተማሪዎቹ በታሪኩ ላይ ያለውን ሰው ምሳሌ እንዲከተሉ አበረታቷቸው።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>
**አሳዩ:** ስዕል፡- ኢየሱስ አስሩን ለምፃሞቸ ፈወሰ።

</td></tr>
<tr><td>የመማር ጊዜ</td><td>

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***መዝሙር 107: 21*** አብራሩ።የማይታወቁ ቃላትን አብራሩ።

</td></tr>
<tr><td>የክለሳ ጊዜ</td><td>

ከፈተና ይልቅ ልጆቹ የሆነ የሚያመሰግኑበትን ነገር ቀለል በሚል ስዕል እንዲያስቀምጡት አድርጉ። አንዳንድ ተማሪዎች እግዚአብሔር ሆይ እናመሰግንሃለን የሚል ፅሁፍ ከስዕሎቹ መሃል በመለጠፍ ከለር እንዲቀቡ አድርጉ።<br>
ትንሽ ቡድን ያላቸው አነስ ያሉ ተማሪዎች አስሩን ለምፃሞች የሚወክሉ 10 ቀለል ያሉ ስእሎችን ይሳሉ።

</td></tr>
</table>

<u>ለ3 ታሪክ 1</u>

**ከኢየሱስ መማር - ይህ ታሪክ ከኢየሱስ ለመማር ጊዜ ስለመውሰድ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው:**<br>• ኢየሱስን መስማትና ከእርሱ መማር በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።<br>• መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ኢየሱስን ልንሰማ ይገባል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 10: 42***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 10: 38-42*** |
| መግቢያ | **አንዱን ሃሳብ ምረጡ:**<br>• ቤት ውስጥ እንግዳ ሲመጣ እናታችሁ እንዴት ምግብ በመስራትና የመሳሰሉትን ነገሮች እንደምትዘጋጅ አውሩ።<br>• ለተማሪዎች ስለሚጠቅሙ ሁኔታዎች አውሩ፡ የት ነው መስማት በጣም አስፈላጊ የሚሆነው? አዲስ ነገር በምንማር ጊዜ፣ አቅጣጫዎችን በምንቀበል ጊዜ …<br>• በትንሽ ቡድን በመሆን ጨዋታ ልትጫወቱ ትችላላችሁ። አንድ መሪ የሆነ መልእክት በመጀመሪው ሰው ጆሮ ይናገራ፣ ይህም ሰው ለቀጣዩ ሰው ይናገራል እንደዚህ እያለ ይቀጥላ የመጨረሻው ሰው የሰማውን ነገር ይደግማ ጨዋታው ጥሩ ሰሚ የመሆንን አስፈላጊነት ይናገራል። ከዛሬው ታሪክ ጋር አገናኙት። የዛሬው ታሪክ አንድ ጊዜውን በመስማት በአግባቡ ስላሳለፈ ሰው ነው። |
| የማስተማር ጊዜ | • ማርታ እና ማርያም የኢየሱስ ጥሩ ጓደኞች ነበሩ። አንድ ቀን ማርታ ኢየሱስን እና ደቀመዛሙርቱን ለምግብ *ጋበዘቻቸው። ተማሪዎቹ የማርታን ዝግጅት እንዲያስቡ አድርጉ ወይንም ከላይ ካለው ከመጀመሪያው ሀሳብ ጋር አገናኙት። የእንግዶቹን መምጣት በውስጣችሁ ሳሉት።* ***(ሉቃስ 10: 38)***<br>• ማርታ ገና ብዙ ስራ ይቀራት ነበር። ምግብ ማዘጋጀቷን ቀጠለች እህቷ ማርያም ደሞ ከኢየሱስ እግር ስር ቁጭ ብላ እየሰማች እና እየተማረች ነበር። *ማርታ ምን ሊሰማት እንደሚችል አስረዱ … ማርታ የተጠቀመችውን እራሱን ቃል ተጠቀሙ።* ***(ሉቃስ 10: 39-40)***<br>• ኢየሱስም ለማርታ መዋከብና መናደድም እንደሌለባት ቀስ ብሎ ነገራት። *ማርታ ለኢየሱስ በጣም ጥሩ ምግብ ለማዘጋጀት መፈለጓ ጥሩ ነገር ቢሆንም እንኳን የመጀመሪያው በጣም አስፈላጊ ነገር ግን እንዳልሆነ አስረዱ።* ማን ነበር የተሻለውን ነገር እያደረገ የነበረው? አዎ ማርያም ነበረች! ኢየሱስ ማርያም የሚበልጠውን ነገር እንደመረጠች እና ከእሷም እንደማይወሰድባት ተናግሯል። ***(ሉቃስ 10: 41-42)***<br>• *ማርያም የመረጠችው የተሻለ ነገር ምንድን ነው? ማርያም ኢየሱስን መስማት በመቻሏ በጣም እድለኛ ነበረች። እኛም መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከኢየሱስን በመስማት እና በመማር እንዴት ጊዜ ማሳለፍ እንዳለብን አውሩ። ይህን በማድረግ እርሱን የበለጠ ማወቅ እና የሚያስደስተውን ነገር መለየት እንችላለን። ተለቅ ከሚሉት ልጆች ጋር ይሄን እንዴት ቅድሚያ ሊሰጡት እንደሚችሉ መነጋገር ትችላላችሁ።*<br><br>የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።<br>**አሳዩ:** ማርታ ስትሰራ፡- |
| የመማር ጊዜ | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ሉቃስ 10: 42*** አብራሩ። ማርያም ስለ መረጠችው ጠቃሚ ምርጫ አሳውቁ። |
| የክለሳ ጊዜ | ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ<br>• እህትማማቾቹ የት ነበር የሚኖሩት?<br>• እንግዶቹ እነማን ነበሩ?<br>• ከኢየሱስ ጋር ጊዜ ያሳለፈችው እህት ማን ትባላለች?<br>• ኢየሱስን ለማስተናገድ የፈለገችው እህት ማን ትባላለች?<br>• የትኛዋ እህት ናት የተናደደችው?<br>• በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትኛው ክፍል ላይ ነው ይሄ ታሪክ የሚገኘው?<br>• ለምንድን ነው ማርታ የተናደደችው?<br>• ኢየሱስን እንዴት ልንሰማው እንችላለን?<br>• የየትኛዋን እህት ምሳሌ ነው ልንከተል ሚገበው?<br>• ማርታ ለማን ነበር ቅሬታዋን የተናገረችው? |

## ለ3 ታሪክ 2

**ህይወት በኢየሱስ - ይህ ታሪክ ኢየሱስ አንድን ሰው ከሞት ሲያስነሳ የሚያሳይ ነው።**

| | |
|---|---|
| | ***የምንማረው:***<br>• ኢየሱስ አልዓዛር ወደ ህይወት ለመመለስ ኃይል ነበረው።<br>• ኢየሱስን ካመንነው ዘላለማዊ ህይወት ይሰጠናል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 11: 25***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዮሐንስ 11: 1-7፣ 17-44*** |
| *መግቢያ* | • ለደረጃ 1-እግዚአብሔር ሰዎችን እንዴት ቤተሰብ ውስጥ እንደሚያስቀምጥ ተወያዩ። ስለ እህቶች እና ስለ ወንድሞች አውሩ። እህት ወይም ወንድም ሲኖር ምንድን ነው ጥቅሙ? ተማሪዎች የባለፈው ሳምንት ታሪክ ላይ የነበሩትን ሁለት እህትማማቾች እንዳስታወሷቸው ጠይቁና አልዓዛርን አስተዋውቁ።<br>• ለደረጃ2-በህይወታችን ውስጥ ነገሮች እንዴት ከእቅዳችን ውጪ እንደሚሄዱ አውሩ ፤ አንዳንድ ጊዜያት ልንቆጣጠራቸው የማንችላቸው እና ያላሰብናቸው ነገሮች ይፈጠራሉ። ኢየሱስ ግን እንዴት አድርጎ ሁሉንም እንደሚቆጣጠር እና ሁኔታውን ለበጎ እንደሚሰራቸው አውሩ። በዛሬው ታሪክ ላይ ማርያምና ማርታ ከባድ ችግር ውስጥ ናቸው። |
| *የማስተማር ጊዜ* | • የማርየምእና የማርታ ወንድም አልዓዛር በጣም ታሞ ነበር። ኢየሱስ እንዲገኝ ስለፈለጉ መልእክት ላኩለት። አልዓዛር ሊፈውሰው እንደሚችል ያውቁ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ላለመምጣት ወሰነ። *ምን ሊሰማቸው ይችላል? ማርያምና ማርታ ሊረዱት ባይችሉም ግን የተሻለው ነገር ምን እንደሆነ ያውቅ ነበር?* ***(ዮሐንስ 11: 1-6)***<br>• ከትንሽ ጊዜ በኋላ አልዓዛር ሞተ በጨርቅም ተገንዞ በዋሻ ውስጥ ተቀበረ። *መግቢያው ላይም በትልቅ ድንጋይ ተዘጋ። ይሄ መቃብር ተብሎ ይጠራል። ማርያምና ማርታ በዚህ ሰዓት ምን አይነት ስሜት ሊሰማቸው እንደሚችል አስቡት።* ከአራት ቀናት በኋላ ማርታ ኢየሱስ እየመጣ እንደሆነ ስትሰማ ልትገናኘው ወጣች። ኢየሱስ አልዓዛር ድጋሜ በህይወት እንደሚኖር ለማርታ አስረዳት። *ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ተጠቀሙ* ***(ቁጥር 25)*** *እናም ትንሳኤ ማለት አንድን ሰው ከሞት የሚያስነሳው ኃይል እንደሆነ አስረዱ።* ሌላ ማንም ይሄ ኃይል የለውም። ***(ዮሐንስ 11: 17-27)***<br>• ኢየሱስ ከማርያምና ከማርታ ጋር አልዓዛር ወደ ተቀበረበት መቃብር ሄደ። ኢየሱስ ከሃዘኑ የተነሳ አለቀሰ። ከዚያም ድንጋዩን እንዲያነሱት ሰዎቹን አዘዘ። ከፍ ባለ ድምፅም "አልዓዛር ና ውጣ!" ብሎ ጮኸ። በሚያስደንቅ ሁኔታ አልዓዛር በጨርቁ እንደተጠቀለለ ወጣ። ኢየሱስ በዚህ ቀን ለአልዓዛር ህይወቱን መስስጠት እንደሚችል ኃይል እንዳለው አሳየ። ይሄ ተአምራት ኢየሱስ ኃይለኛና ልዩ መሆኑን እንዲያስተውሉ አደረጋቸው። *በዚህ አጋጣሚ ስላስተማራቸው ነገር ሁሉ አውሩ፤ ጊዜውን፣ ሀዘናቸውን መካፈሉን፣ ስለኃይሉ፣ ሁሉን መቆጣጠሩ… ኢየሱስ አልዓዛር ከመሞቱ በፊት ቢመጣ ኖሮ ተአምራቱ አያስፈልግም ነበር።*<br>• የእኛንም ትልቁን ጠላታችንን ሞትን ሊያሸንፍ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ልክ ለአልዓዛር ህይወቱን እንደሰጠው እና ከሞት እንዳስነሳው። በጌታ ኢየሱስ ስናምን የዘላለምን ህይወት ተስፋ ይሰጠናል።<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:** ስዕል:- አልዓዛር ከሞት ተነሳ |
| *የመማር ጊዜ* | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ዮሐንስ 11: 25*** አብራሩ። ኢየሱስ ይህንን ስም ሲጠቀም ስለራሱ ጠቃሚ እውነታን እየነገረን እንደሆነ አስረዱ። የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያላቸው ህፃናት "እኔ እኔ ነኝ" የሚሉትን ዓረፍተ ነገሮች ሊያስታውሱ ይችላሉ። |
| *የክለሳ ጊዜ* | *ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:*<br>• *ማን ነበር በጣም የታመመው?*<br>• *ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ምን ያህል ጊዜ ነበረ?*<br>• *ኢየሱስን ለመገናኘት የወጣችው የትኛዋ እህት ነበረች?*<br>• *ኢየሱስ ማርታን ሲያወራ ለራሱ የተጠቀመው ስም ምን ነበር?*<br>• *ኢየሱስ የአልዓዛር መቃብር ጋር ምን እንደተሰማው እንዴት ነበር የገለፀው?*<br>• *ምን ነበረ የተናገረው?*<br>• *ኢየሱስ በዚያ ቀን ለሁሉም ያረጋገጠው ነገር ምን ነበር?*<br>• *እንዴት ነው ዘላለማዊ ህይወት ሊኖረን የሚቸለው?* |

# <u>ለ3 ታሪክ 3</u>

**ፍቅር ለኢየሱስ - ይህ ታሪክ ማርያም ፍቅሯን ለኢየሱስ ስትገልጥ የሚያሳይ ነው።**

| | |
|---|---|
| | ***የምንማረው:***<br>• *ማርያም ባደረገችው ነገር ለኢየሱስ ፍቅሯን አሳየች።*<br>• *ኢየሱስ ላሳየን ፍቅር ምላሽ እኛም ልንወደው ይገባል።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***1 ዮሐንስ 4: 19***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዮሐንስ 12: 1-11*** |
| *መግቢያ* | ስለ ምስጋና እና ስጦታዎች አውሩ። ከተቻለ በእናንተ ባህል የተለመዱ ስጦታዎች ብትይዙና ለማን ቢሰጥ ጥሩ ይሆናል የሚለውንም ለማሳየት ብትጠቀሙ የተመረጠ ነው።<br>ያለፈውን ሳምንት ታሪክና ማርያም፣ ማርታና አልዓዛር እንዴት በምስጋና ውስጥ እንደነበሩ ተማሪዎችን አስታውሱ። |
| **የማስተማር ጊዜ** | • *ማርታ፣ማርያምና አልዓዛር ለኢየሱስ ድግስ ለመደገስ አሰቡ። እስቲ ሳሉት፡ ቤቱ በእንግዶች ተሞልቶ፣ አልዓዛር ጤነኛ ሆኖ ቆሞ፣ ኢየሱስ የክብር እንግዳ ሆኖ፣ ማርታ እያስተናገደች ... **(ዮሐንስ 12: 1-2)***<br>• በድግሱ ሰዓት ማርያም በጣም ውድ ሽቱ ይዛ ኢየሱስ አጠገብ መጣች። ከዚያም ኢየሱስ እግር ላይ አፍስሳ በፀጉሯ አበሰችው። *ሁሉም ምን እየተፈጠረ እንዳለ ለማየት ትኩረታቸው ሲሳብ እና ሽቱው በጣም ሲሸታቸው ያለውን ነገር ግለፁ። ማርያም ይህን ያደረገችው ኢየሱስን በጣም ስለምትወደው እንደሆነ አስረዱ፤ ኢየሱስ ለእርሷ ከምንም ነገር በላይ ዋጋ ነበረው። **(ዮሐንስ 12: 3)***<br>• የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ከነበሩት ውስጥ አንዱ (ይሁዳ) ማርያም ለምን ሽቱውን እንዳፈሰሰች አልገባውም ነበር። እሱ ልክ እንደ ኪሳራ ነበር የቆጠረው! *ይሁዳ የተናገረውን ቃል ተጠቀሙ እና ምን አይነት ሌባ እና ስግብግብ ሰው እንደነበረ አስረዱ። (የደረጃ 2 ትምህርት) **(ዮሐንስ 12: 4-6)***<br>• ይሁዳ እና ማርያም ለኢየሱስ ያሳዩት የተለያየ አይነት አመለካከት ነበር። ይሁዳ የኢየሱስን ታላቅነት ካለማወቁም በተጨማሪ በልቡ ውስጥ ለኢየሱስ ምንም ፍቅር አልነበረውም። በተቃራኒው ደግሞ ኢየሱስ ለማርያም በጣም የከበረና ተወዳጅ ነበር። ባደረገችው ነገርም ኢየሱስ ተደስቷል። ***(ዮሐንስ 12: 7-8)*** *የማንን ምሳሌ ነው ልንከተል የሚገባው?*<br>• *ኢየሱስ እኛን ምን ያህል እንደወደደንና እኛን ለማዳን ህይወቱን እንደሰጠን በማሰብ ለእርሱ ትልቅ ዋጋ ሊኖረን ይገባል። እርሱ በወደደን ልክ እንደ ማርያም እኛም ልንወደው እንችላለን። ፍቅራችንን ልንገልፅባቸው ምንችላቸውን መንገዶች አውሩ፡- እርሱን ማመን፣ በፀሎት እና ቃሉን በማንበብ ከእርሱ ጋር ጊዜን ማሳለፍ፣ለእርሱ መታዘዝ፣ ሌሎችን በመውደድና ስለ እርሱ በመናገር።*<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:** ስዕል፡- ኢየሱስን ሽቱ ስትቀባው። |
| **የመማር ጊዜ** | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***1 ዮሐንስ 4: 19*** አብራሩ። *ተማሪዎቹ "እሱ" የሚሉት ተውላጠ ስሞች ማን ማንን እንደሚያመለክቱ ማወቃቸውን አረጋግጡ።* የእኛ ፍቅር እርሱ ለእኛ ካለው ፍቅር የመነጨ እንደሆነ አብራሩ። |
| **የክለሳ ጊዜ** | *ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:*<br>• *ድግሱ የት ነበር የተካሄደው?*<br>• *በዚያ ቦታ በጣም ተፈላጊው ሰው ማን ነበር?*<br>• *ማርያም ምን ነበር ያደረገችው?*<br>• *ለምን ነበር ማርያም ይህን ያደረገችው?*<br>• *ማርያም ኢየሱስ ላይ ሽቱውን ስታፈስ ይሁዳ ምን ነበር ያለው?*<br>• *ጌታ ኢየሱስን ለምንድን ነው መውደድ ያለብን?* |

<u>**ለ3 ታሪክ 4**</u>

**ኢየሱስን ማየት - ይህ ታሪክ ኢየሱስን ስለ መቀበል ነው።**

**የምንማረው:**
- ኢየሱስ ልዩ ነው፤ የነገስታት ንጉስ ነው።
- ጌታ ኢየሱስን ወደ ህይወታችን ልንጋብዘው ይገባል።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 1: 12***
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 19: 28-44***

***መግቢያ***

አስፈላጊ ጎብኚዎች ምን አይነት አቀባበል እንደሚደረግላቸው አውሩ ለምሳሌ፡የንጉስ ቤት ጎብኚዎች፣ ፕሬዝዳንት፣ የስፖርት ተወዳዳሪዎች፣ ት/ቤት ሚጎበኝ ሰውከተቻለ ስእሎችን ተጠቀሙ። በግርግር መሀል መሆን ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡት።
በዚህ ጊዜ ልዩ ጎብኚው ኢየሱስ እንደነበረ አስረዱ። ወደ እየሩሳሌም ከተማ ለመጨረሻ ጊዜ እየገባ ነበር ምክያቱም በቅርብ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈፅሞ ለእኛ ኃጢአት ሊሞት ነበር። ኢየሱስ ምን ያህል ልዩ እንደሆነ ሰዎች እንዲያውቁ እግዚአብሔር ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን “የጌቶች ጌታ እና የነገስታት ንጉስ” ይለዋል። እግዚአብሔር ይህንን ቀን ወደ እየሩሳሌም ሲገባ ሰዎች ኢየሱስን እንዲያዩት እቀዱ ነበር።

***የማስተማር ጊዜ***

- ኢየሱስ እና ደቀ መዝሙሩቱ ወደ እየሩሳሌም እየቀረቡ ሲመጡ ሁለቱን ወደ ሰፈሩ እንዲሄዱ ላካቸው። ሰፈር ውስጥ የታሰረች ውርንጫ ሲያገኙ ፈተው እንዲያመጧትና ሰዎች ምን እያደረጉ እንደሆነ ከጠየቋቸው “ለጌታ ያስፈልገዋል” ብለው እንዲመልሱ አዘዛቸው። ***(ሉቃስ 19: 28-31)***
- *ደቀመዛሙርቱ ውርንጫዋን ፈተው ወደ ኢየሱስ ይዘዋት ሲመጡ እንዴት እንደሆነ አስቡት። ሰው ተቀምጦበት የማያውቅ ውርንጫ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀመጡበት እንዴት ነው ምላሽ የሚሰጠው? ደቀመዛሙርቱ የውርንጫዋ* ጀርባ ላይ ኮት አነጥፈው ኢየሱስ ያለምንም ችግር ተቀመጠባት። እርሱ በሁሉም ፍጥረቶች ላይ ኃይል አለው። ***(ሉቃስ 19: 32-35)***
- ልክ ኢየሱስ መሄድ ሲጀምር ብዙ ሰዎች እየመጡ በመንገድ ላይ ኮታቸውን እንደ ምንጣፍ አነጠፉ። አሁን ሰዎቹ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ያውቃሉ፤ በእግዚአብሔር የተላከ ልዩ ንጉስ። *ገስታት ወደ ጦርነት ሚሄዱት በፈረስ እየጋለቡ ነበር ነገር ግን ኢየሱስ በአህያ ላይ በመሄዱ ሰላምን ይዞ መምጣቱን እንደሚወክል አብራሩ።* ሰዎቹ በጉጉት እየጮኹ እግዚአብሔርን እያከበሩ “በጌታ ስም የሚመጣ እርሱ የተባረከ ይሁን” እያሉ ነበር። ***(ሉቃስ 19: 36-38)***
- *ኢየሱስን የማይወዱትና አቀባበል እየተደረገለት እንደሆነ ሲየዩ የተናደዱም እንዳሉ ጥቀሱ።* ***(ሉቃስ 19: 39-40)*** እነዚህ ሰዎች በቅርቡ መንገድ አጊኝተው ኢየሱስን ለሞት እንደሚያቀርቡት ያውቅ ነበር።
- *ስለ ኢየሱስ የምናደርገው ጠቃሚ ምርጫ እንዳለ ተማሪዎችን አሳውቁ። ወደ ህይወታችን ልንቀበለው እንችላለን ወይንም ደግሞ “እንቢ” ብለን ምንም ቦታ ላንሰጠው እንችላለን። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ወደ ህይወታችን እንድንጋብዘው ይፈልጋል። ይህን ስናደርግ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል እንሆናለን።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**
**አሳዩ:** የሚሆን ስዕል የለም :-.

***የመማር ጊዜ***

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ዮሐንስ 1: 12*** አብራሩ። መቀበል ወይም ማመን የሚሉት ቃላቶች አንድ አይነት ሀሳብ ነው የሚወክሉት። “እሱ” የሚሉት ተውላጠ ስሞችን በደንብ እንደተረዷቸው አራግጡ።

***የክለሳ ጊዜ***

ቀጥሎ ያሉትን እውነት ወይም ሀሰት ዓረፍተ ነገሮች ለመፈተን ተጠቀሟቸው:
- ኢየሱስ እና ደቀመዛሙርቱ ወደ እየሩሳሌም እየገቡ ነበር።
- ኢየሱስ ሶስቱን ደቀ መዛሙርት ወደ አንድ ሰፈር ላካቸው።
- በአህያው ተቀምጠው ነበር።
- ኢየሱስ አህያው ላይ ሲቀመጥ አህያው አልተወራጨም ነበር።
- ሰዎች መሬት ላይ ምንጣፍ እያነጠፉ ነበር።
- ሁሉም ኢየሱስን ተቀበሉት።
- ኢየሱስ የነገስታት ንጉስ ነውና ልንቀበለው ይገባል።
- ኢየሱስን ወደ ህይወታችን ስናስገባው የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል እንሆናለን።

<u>**ለ4 ታሪክ 1**</u>

**የኢየሱስ ሞት - ይህ ታሪክ የኢየሱስ ስለ እኛ መሞት ነው።**

<table>
<tr><td></td><td>

**የምንማረው:**

- ኢየሱስ ሊሰቃይና ሊሞት አይገባውም ነበር።
- ኢየሱስ የሞተው ከኃጢአታችን ሊያድነን ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 23: 33***<br>
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 23:1-26, 32-43***

</td></tr>
<tr><td>*መግቢያ*</td><td>

ካርዶች ላይ እነዚህን ነገሮች ጻፉ፡ በጓደኛ የተከዳ፣ በሀሰት የተከሰሰ፣ የተሳቀበት፣ **የሆነሰው መጥፎ የሆነበት።** ከየቀን ህይወታችሁ ምሳሌ ስጡ ወይንም በትንሽ ቡድን በመሆን ተማሪዎች ከራሳቸው የህይወት ተሞክሮ እንደዚህ አይነት ነገር ሲደረርስባቸው ስሜታቸው እንዴተ እንደሆነ ይነጋገሩ። እንዲህ እንዳይቀጥል ለማቆም እንሞክራለን!<br>
ኢየሱስ ሰው ሲያመናጭቀን ስሜቱ እንዴት እንደሆነ ያውቃል። ሰዎች ይህንን እና ሌላም የባሱ ነገሮች አድርገውታል። ኢየሱስ ለምን እንደዚህ እንደተሰቃየ ዛሬ እናያለን።

</td></tr>
<tr><td>የማስተማር ጊዜ</td><td>

ትምህርት ቤት ውስጥ የምታስተምሩ ከሆነ አግድም መስመሮችን በመጠቀም በጊዜ ቅደም ተከተል ብታስቀምጡት ጥሩ ነው።ካርዶች ላይ በመፃፍ ተጠቀሙ፤ የመጨረሻው እራት፣ ጸሎት በአትክልት ስፍራው፣ በጠላቶች መታሰር፣ በጲላጦስ መጠየቅ፣ የተናደደው ህዝብ፣ ለመሰቀል ሲወሰድ፣ ሶስቱ መስቀሎች፣ ይቅር የተባለው ወንበዴ …እነዚህ ድርጊቶች ታሪኩ በዝርዝር እንዴት እንደሄደ ያሳዩናል።

- *ወደ እየሩሳሌም ሲገባ የነበረውን ነገር ልጆቹን ለማስታወስ ጥቂት ጥያቄዎችን ጠይቋቸው።* ከጥቂት ቀናት በኋላ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ያለውን የመጨለሻ እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አደረገ። ቀጥሎም ለመፀላይ ወደ አትክልት ስፍራው ሄደ። *የነበረውን ነገር ለማሳየት ተዘጋጁ፤ ጨለማው፣ ፀጥታው፣ ቀጥሎም የኮቴ ድምፅና የይሁዳ ከሚያስሩት ሰዎች ጋር መተባበር። ኢየሱስ በዚያ ሰአት ሊሰማው የሚችለውን ሀዘን ግለፁ።*
- በቀጣዩ ቀን ኢየሱስን ወደ አስተዳደሩ ወደ ጲላጦስ ወሰዱት። ***(ሉቃስ 23: 1-4, 20-25)*** *የእርሱን የስልጣን ደረጃ እና ኢየሱስ ላይ ምንም ጥፋት ሊያገኙበት እንዳልቻለ አተኩራችሁ አስረዱ። ኢየሱስ ፃድቅና ምንም ኃጢአት የሌለበት ነበር።* በመጨረሻም ጲላጦስ ህዝቡ የፈለገውን ነገር በማድረግ ኢየሱስ ላይ የሞት ትእዛዝ አወጣ። *ለእኛ ፍትሐዊ ያልሆነ ስራ የተሰራ ይመስላል ነገር ግን ሁሉንም ነገር እኛን ለማዳን እግዚአብሔር በእቅድ ነው ያደረገው።*
- ኢየሱስ ከእየሩሳሌም ውጪ ተወሰደ። ስምኦን የተባለን አንድ ሰው የሚከብደውን የእንጨት መስቀል እንዲሸከም አስገደዱት። ***(ሉቃስ 23: 26)*** ተራራው ጫፍ ላይ ሲደርሱ ኢየሱስን በሚስማር እንጨቱ ላይ አጣበቁት። ከኢየሱስ በሁለቱም ጎን ደግሞ ሁለት ወንበዴዎች ተሰቀሉ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ ወታደሮቹና ሰዎቹ ቀለዱበት። አጠገቡ የተሰቀለው አንዱ ወንበዴ እንኳን መጥፎ ንግግር ተናገረ። አንደኛው ሌባ ግን ኢየሱስ እንደነሱ አይነት ሰው እንዳልሆነ ያውቅ ነበር። እነሱ በጥፋታቸው እንደተሰቀሉ ኢየሱስ ግን ያለምንም ጥፋት እንደተሰቀለ ገብቶታል። ኢየሱስ ማን እንደሆነ ስላስተዋለም በመንግስቱ እንዲያስበው ጠየቀው። በዛኑ ቀን ኢየሱስ በገነት ከእርሱ ጋር እንደሚያኖረው ቃል ገባለት። ***(ሉቃስ 23: 32-43)***
- *ልክ እንደ አንዱ ወንበዴ ኢየሱስ ሞት እንደማይገባው ልንረዳ ይገባል። ኢየሱስ የተሰቃየውና የሞተው የእግዚአብሔርን ትልቅ ፍቅር ሊያሳየንና የኃጢአታችንን ቅጣት ለመውሰድ ነው። ይቅር እንዲለን ከለመነው አንድ ቀን በገነት እንደምንኖር እርግጠኞች መሆን እንችላለን።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>
**አሳዩ:** ስዕል፡- የኢየሱስን ስቅለት እና ሞት የሚያሳዩትን ብትጠቀሙ ጥሩ ነው።

</td></tr>
<tr><td>የመማር ጊዜ</td><td>

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ሉቃስ 23: 33*** እንደየልጆቹ አቅም አብራሩ። ኢየሱስ የሞተበትን ተራራ ስም አስረዱ።

</td></tr>
<tr><td>የክለሳ ጊዜ</td><td>

ፅሁፎቹን ቀላቅሉና ልጆቹ በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጧቸው አድርጉ። የምትሰሩት ከትናንሽ ቡድኖች ጋር ከሆነ ብዙ ኮፒዎችን ያዙና ቀድሞ የጨረሰው ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

</td></tr>
</table>

<u>**ለ4 ታሪክ 2**</u>

## ኢየሱስ ሞተ እና ተቀበረ - ይህ ታሪክ ስለ ኢየሱስ መሞት እና መቀበር ነው።

**የምንማረው:**

- የኢየሱስ ሞት ከሌላው ሞት ይለያል ምክንያቱም የኛን ቅጣት ነበር የወሰደው።
- ለእኛ ስላለው ትልቅ ፍቅር ልናመሰግነው ይገባል።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***1 ቆሮንጦስ 15: 3 እና 4***
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 23: 44-56***

### መግቢያ

ስለ ቀን እና ስለ ምሽት አንዱ ሌላውን እንዴት እንደሚከተል አውሩ። ምሽትን በተወሰነ ሰዓት ላይ እንጠብቃለን! እግዚአብሔር እንደዚህ እንዲሆን ነው የፈጠረው።ነገር ግን ኢየሱስ የሞተበት ቀን የተለየ ነበር። በድንገት ያለምንም ማስጠንቀቂያ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ ፀሀይ ማብራት አቁማ ጨለማ ሆነ። ***(ሉቃስ 23: 44, 45)*** እግዚአብሔር ለምን ይህ እንዲፈጠር አደረገ?

### የማስተማር ጊዜ

- *በእነዚህ ሶስት ሰዓታት ኢየሱስ ስለ እኛ ኃጢአት በእግዚአብሔር እንደተቀጣ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ባለፈው ሳምንት ታሪክ ኢየሱስ ምን ያህል እንደተሰቃየ ልጆቹ እንዲያስታውሱት ጠይቋቸው። ስቃዩን በትንሹ ልንረዳው እንችል ይሆናል ለኃጢአታችን የተቀጣውን ቅጣት ግን መቼም ልንረዳው አንችልም። ኢየሱስ ይህን በፈቃደኝነት ያደረገው በጣም ስለሚወደንና እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ያለውን እቅድ ለመፈፀም ነው።*
- በመጨረሻም ኢየሱስ መንፈሱን ለእግዚአብሔር አደራ ሰጠ። ***(ሉቃስ 23: 46)*** ኢየሱስ ይህን ያለው አባቱ እንዲሰራ የላከውን ስራ መፈፀሙን ለማሳየት ነበር። *የሆነን ስራ እንዳጠናቀቅንና ሌላ ምንም ሚሰራ ስራ እንደሌለ ስናውቅ ምን ያህል እርካታ እንዳለው ጥቀሱ ምሳሌ፡ዲዛይን መስራት። ኢየሱስ ኃጢአታችን ይቅር እንዲባል ሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ሰርቷል። ኢየሱስ እነርሱን ወክሎ ላደረገው ነገር ምን ምላሽ ሊሰጡ እንደሚገባ ልጆቹን አወያዩ።*
- ከዚያም ኢየሱስ ሞተ። *ጓደኞቹ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል አስቡት።* አንድ ዮሴፍ የሚባል ደግ ጓደኛ ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን አስከሬን እንዲሰጡት ጠየቀ። በጥንቃቄ ከመስቀል ላይ አውርዶ በጨርቅ ጠቅልሎ በመቃብር ውስጥ አኖረው። *መቃብሩ ልክ እንደ ትንሽ ዋሻ እንደነበር አብራሩ።* ከዚያም ትልቅ ድንጋይ መግቢያው ላይ አኖረ። ***(ሉቃስ 23: 50-53)***

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**
**አሳዩ:** ስዕል፡- - ፎቶግራፎቹ ለዚህ ቡድን አይሆኑም ነገር ግን የኢየሱስን ስቅለት እና ሞት የሚያሳዩትን ብትጠቀሙ ጥሩ ነው።

### የመማር ጊዜ

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***1 ቆሮንቶስ 15: 3 እና 4*** ። አነስ ያሉት ህፃናት የመጀመሪያዎቹን አምስት ቃላት ሊናገሩ ይችላሉ። ልጆቹ ቅዱሳት መጽሐፍቶች ምን እንደሆኑ እንደሚያውቁ እርግጠኞች ሁኑ እና ኢየሱስ ላይ የሆነው ነገር ሁሉ ከመቶ አመታት በፊት በብሉይ ኪዳን ላይ የተፃፈ መሆኑን አስረዱ።

### የክለሳ ጊዜ

ቀጥሎ ያሉትን እውነት ወይም ሀሰት ዓረፍተ ነገሮች ለመፈተን ተጠቀሟቸው:

- ጨለማው የጀመረው በቀኑ መሀል ነበር።
- ለአራት ሰአታት ነበር የቆየው።
- በጨለመበት ሰዓት ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ወሰደ።
- ከመሞቱ በፊት ኢየሱስ ከአባቱ ጋር አውርቷል።
- የኢየሱስ ጓደኞች ኢየሱስ የሆነው ነገር ሁሉ ገብቷቸው ነበር።
- ዮሴፍ የኢየሱስን አስከሬን እንዲሰጡት ወታደሮቹን ጠይቆ ነበር።
- አስከሬኑ በላይነን ጨርቅ ነበር የተገነዘው።
- አስከሬኑን ባረጀ መቃብር ውስጥ ነበር ያኖረው።

## ለ4 ታሪክ 3

### የኢየሱስ ከሞት ተነሣ- ይህ ታሪክ ኢየሱስ በህይወት መኖሩን ማርያም ማወቋን ነው።

**የምንማረው:**

- ኢየሱስ በሞተ በሶስተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሳው።
- እኛም ልክ እንደ ማርያም የተነሳውን ጌታ ማግኘት እንችላለን።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሮሜ 10: 9***

**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዮሐንስ 20: 1-18***

**መግቢያ**

ባለፈው ታሪክ ላይ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን ነበር የተማርነው። ለእኛ ይሄ መልካም ዜና እንደሆነ አብራሩ። በኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት እግዚአብሔር የእኛ ኃጢአት ይቅር የሚባልበትን መንገድ አዘጋጀ። የእግዚአብሔር አስገራሚ እቅድ ተፈፅሟል።
የኢየሱስ ጓደኞች ግን ተናደውና አዝነው ነበር። እኛ አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል የተረዳናቸውን ነገሮች እነሱ በዚያን ጊዜ ሊገባቸው አልቻለም ነበር። ሀዘናቸው ግን ብዙ ጊዜ አልቆየም። ይህ ታሪክ በጣም ደስ የሚል መዝጊያ አለው።

**የማስተማር ጊዜ**

- *ስለ ኢየሱስ ቀብር፣ ስለመቃብሩ እና መቃብሩ ስለተዘጋበት ትልቁ ድንጋይ ልጆቹን አስታውሱ። አሁን እሁድ ማለዳ ኢየሱስ ከሞተ ሶስተኛው ቀን ነበረ። የኢየሱስ ጥሩ ጓደኛ የነበረችው ማርያም መቃብሩን ለማየት ሄደች። ድንጋዩ ተንከባሎና መቃብሩ ባዶ ሆኖ ስታገኘው ምን ያህል ልትደነግጥ እንደምትችል አስረዱ። ማርያም ጴጥሮስንና ዮሐንስን አግኝታ ምን እንዳየች ለመናገር ሮጠች። እሷ ያወራችውን ቃላት ተጠቀሙ።* ***(ዮሐንስ 20: 1-2)*** *ስለዚህ ዜና ምን ሊሰማቸው ይችላል?*
- ጴጥሮስና ዮሐንስ በሰሙት ዜና ተገርመው ለማየት የሚችሉትን ያህል በፍጥነት እየሮጡ ሄዱ። ዮሐንስ መጀመርያ ደርሶ ወደ ውስጥ ተመለከተ። ጴጥሮስ ግን ገና እንደደረሰ ቀጥታ ወደ ውስጥ ገባ። የኢየሱስ አስክሬን የተጠቀለለበት ጨርቅ ብቻ ነበረ። ዮሐንስም ወደ ውስጥ ገባ። በፍጥነትም ዮሐንስ ምን እንደተፈጠረ አወቀ። ኢየሱስ በህይወት እንዳለ አወቀ! ***(ዮሐንስ 20: 3-9)***
- ነገር ግን ማርያም ግራ ገብቷት ነበር። ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ከሄዱ በኋላም ማርያም በአትክልት ስፍራው ቆየች። ቆማ አለቀሰችና በድጋሜ ወደ መቃብሩ ውስጥ አየች። በዚህ ሰዓት ማርያም በድጋሜ ተደነቀች። *ማርያምን ከሁለቱ መላእክቶች ጋር የተነጋገረችውን ንግግር አገናኙና አብራሩ።* ***(ዮሐንስ 20: 10-13)***
- በመቀጠል ማርያም ወደኋላ ዞረች። የማታውቀው ሰው በአትክልት ስፍራው ቆሞ ነበር። በዚያ ጊዜ ያ አዲስ ሰው ስሟን ጠራ "ማርያም!" በድንገት ድምፁን አወቀችው።ጌታዋ ነበር ጌታ ኢየሱስ! *ማርያም አሁን ምን ሊሰማት ይችላል?* ማርያም በደስታ ተሞላች! ኢየሱስን ራስዋ አየችው። የእውነትም በህይወት ነበረ! ለሁለተኛ ጊዜ ማርያም ደቀ መዝሙሩቱን ለማግኘት ሄደች። *በዚህ ሰዓት ምንድን ነው የምትነግራቸው?* ***(ዮሐንስ 20: 14-18)***
- *እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት አስነስቶታል። ዛሬ እርሱ ህያው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ዘላለም ህያው እንደሆነ ይናገራል። ማርያም መቃብሩ ጋር ኢየሱስን ስታገኘው በጣም እንደተደሰተችው ሁላ የእኛንም ህይወት በደስታ ሊሞላው ይፈልጋል። ኢየሱስን እንደ ጓደኛ መቅረብና ስለሚሰጠን ይቅርታ፣ኃይልና ደስታ ከተማሪዎች ጋር ተወያዩ።*

የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።
**አሳዩ:** ስዕል፡- ኢየሱስ ከሙታን ተነሳ

**የመማር ጊዜ**

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ሮሜ 10: 9*** አብራሩ። *"መመስከር" ማለት ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ማመናችንን ለሌሎች ማሳወቅ ማለት እንደሆነ አስረዱ። ይሄ ጥቅስ የሚያስተምረን እግዚአብሄሐር ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው ከኃጢአት ቅጣት እኛን ነፃ ለማድረግ እንደሆነ ማመን እንዳለብን ነው።*

**የክለሳ ጊዜ**

*ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:*

- *ወደ መቃብሩ መጀመርያ የሄደው ማን ነበረ?*
- *ማርያም ድንጋዩን ምን ሆኖ ነበር ያየችው?*
- *ሄዳ ለማን ነበር የተናገረችው?*
- *ወደ መቃብሩ ማን ነበረ መጀመርያ የገባው?*
- *ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ አለመኖሩን ካየ በኋላ ዮሐንስ ምን ነበር ያደረገው?*
- *ማርያም በመቃብሩ ውስጥ ብቻዋን በነበረች ጊዜ ምንድን ነው ያየችው?*
- *መላእክቶቹ ማርያምን ምን ነበር የጠየቋት?*
- *በአትክልት ቦታው ከማርያም ጋር የነበረው ማነው?*
- *ኢየሱስ መሆኑን እንዴት አወቀች?*
- *ኢየሱስን ከሞት ያስነሳው ማን ነበር?*

## ለ4 ታሪክ 4

**የኢየሱስ መሄድና መመለስ - ይህ ታሪክ ስለ ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ መምጣት ነው።**

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው:**<br>• ኢየሱስ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄዷል አሁንም በዚያ ነው ያለው።<br>• ተመልሶ ሲመጣ ዝግጁ መሆን አለብን።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሐዋ. ስራ 1: 11***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 24: 50-53፣ ሐዋ.ስራ 1: 4-12*** |
| *መግቢያ* | ቻው ቻው ስለ ማለት በድራማ መልክ በማቅረብ አሳዩ። ለምሳሌ-አንድ ዘመድ ከብዙ ቆይታ በኋላ ከእናንተ ሲለይ፣ የክፍላችሁ ተማሪ ወደ ሩቅ ቦታ ሲሄድ ወይንም ከራሳችሁ የህይወት ተሞክሮ አካፍሉ። የሚሄደው ሰው ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል ሊገባ ይችላል። ይህ ቃል መለየቱን ትንሽ ያቀለዋል። |
| **የማስተማር ጊዜ** | • ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ደስ የሚል ጊዜ አሳለፉ። አሁን ለምን እንደሞተ የተሻለ መረዳት አላቸው። ከስድስት ሳምንታት በኋላ አስራ አንዱን ደቀመዝሙርት ይዞ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ወጣ። ወደ ገነት መመለሻው ጊዜ እንደደረሰ አስረዳቸው። ብቻቸውን አይተዋቸውም ምክንያቱም በቅርቡ መንፈስ ቅዱስ የሚባል አፅናኝ ይመጣላቸዋል። *ኢየሱስ እያዋራቸው እያለ በድንገት ከመሬት ከፍ ከፍ አለ። እስቲ ሳሉት ደቀ መዝሙሩቱ ወደ ላይ ሲያዩ ኢየሱስ ከአይናቸው እይታ በደመና ሲሰወር። ኢየሱስ ወደ ሰማይ አረገ ከሚለው ማየት ትችላላችሁ። ምን ሊሰማቸው እንደሚችል አስቡት፡ ግራ መጋባት? መደነቅ? ሀዘን? **(ሐዋ.ስራ 1: 8-9)***<br>• በዚያ ሰዓት ሁለት መላእክቶች ተገልጠው ለምን ቆመው ወደ ሰማይ እንደሚያዩ ጠየቋቸው። ከዛም ልክ እንደ ሄደው ሁሉ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ ነገሯቸው። ***(ሐዋ.ስራ 1: 10, 11)***<br>• ደቀ መዝሙሩቱ ተራራ ላይ መቆየት እንደሌለባቸውና ቃል የተገባላቸውን አፅናኝ ለመቀበል ወደ እየሩሳሌም መሄድ እንዳለባቸው ያውቃሉ። አላዘኑም ይልቁንም በደስታ ተሞልተው ነበር። ***(ሉቃስ 24: 52)*** *መግቢያ ላይ ሰዎች ሲለያዩ ካለው ሀሳብ ጋር አገናኙት። ኢየሱስ ቃሉን እንደሚጠብቅ ደቀ መዛሙርቱ እንዳመኑት ሁሉ እኛም የገባልንን ቃሎች ማመን ያስፈልገናል።*<br>• ኢየሱስ ዛሬም በመንግስተ ሰማይ ነው። እርሱን የሚወዱትም መምጣቱን ይጠባበቃሉ። *መቼ እንደሚሆን አናውቅም ነገር ግን ይሆናል፤ ቃሉን ይጠብቃል። ኢየሱስ ሲመጣ ዝግጁ እንዲሆኑና እንዴት ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው እንደሚያውቁ ልጆቹን ኢየሱስ ኃጢአታቸውን ይቅር እንደሚል በማመን እንዲዘጋጁ አድርጉ።*<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:** ስዕል፡- ኢየሱስ ወደ ሰማይ አረገ |
| **የመማር ጊዜ** | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ሐዋ. ስራ 1: 11*** አስተምሩ። ይሄ ረዥም ጥቅስ ነው፤ ለቡድናችሁ ልጆች የሚመጥን ያክል ቃላት ምረጡና አስተምሩ። ለምሳሌ፤ ለደረጃ 2 "ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ..." ወይንም በደረጃ አንድ እንደተሰጠው የመላእክት ቃላት። |
| **የክለሳ ጊዜ** | ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:<br>• በደብረዘይት ተራራ ላይ ከኢየሱስ ጋር ስንት ደቀ መዝሙርት ነበሩ?<br>• ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የት ሊሄድ እንደሆነ ነበር የነገራቸው?<br>• ምን እንደሚቀበሉ ነበር ቃል የገባላቸው?<br>• ከእይታቸው የሰወረው ምን ነበር?<br>• መላእክቶቹ ምን የሚል መልእክት ነበር የነገሯቸው?<br>• ደቀ መዛሙርቱ ቀጥሎ ወዴት ነበር የሄዱት?<br>• ኢየሱስ መቼ ነው ተመልሶ ሚመጣው?<br>• ኢየሱስ ለማን ነው የሚመጣው? |

<u>ለ5 ታሪክ 1</u>

**ደጉ ሳምራዊ - ይህ ታሪክ አጠገባችን ያለውን ሰው ስለ መውደድ ነው።**

**የምንማረው:**

- ጌታ ኢየሱስ ለሁሉም ሰው ደግ እንድንሆን ይፈልጋል።
- ኢየሱስ ልክ እንደ ደጉ ሳምራዊ ነው። አዳኛችን፣ ጓደኛችን እና ረዳታችን ሊሆን ይፈልጋል።

**ቁልፍ ጥቅስ:** *ሉቃስ 10: 27*
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** *ሉቃስ 10: 25-37*

*መግቢያ*

የሚወዱት ታሪክ ምን እንደሆነ ልጆቹን ጠይቁ (ሰዓት በመቆጠብ ስዕል ስለው ሊገልፁ ይችላሉ)።
ኢየሱስ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር እንዲረዱ የሚያደርጉ ብዙ ታሪኮችን ይናገር እንደነበር ተናገሩ። ስለዚህም የእርሱ ታሪኮች የተለየ ትርጉም ነበር ያላቸው። ከእነዚህ ታሪኮች መሀል አንዳንዶቹን እንሰማለን፡ እነዚህ ታሪኮች ምሳሌዎች ይባላሉ። ልጆቹን ሄደውበት ስለሚያውቁት ረዥም ጉዞ ጠይቋቸው። የት ነበር የሄዱት? እንዴት ነበር የተጓዙት? ጉዞው እንደታሰበው ነበር የሄደው?

**የማስተማር ጊዜ**

- ሰውየው ለጠየቀው ጥያቄ ምላሽ እንዲሆን አንድ ጉዞ ላይ ስላለ ሰው ታሪክ ነገራቸው።ጥያቄውን የጠየቀው ሰው እግዚአብሔርን በፍፁም ልቡ፣ በፍፁም ነፍሱ፣ በፍፁም ሀይሉ፣ በፍፁም ሀሳቡ መውደድ እንዳለበትና ባልንጀራውንም እንደ እራሱ መውደድ እንዳለበት ያውቃል ነገር ግን ምን ማለት እንደሆነ አልገባውም ነበር። ***(ሉቃስ 10: 25-28)*** *ተወያዩ፡ እግዚአብሔርን በፍፁም ልብ፣ በፍፁም ነፍስ፣ በፍፁም ኃይልና በፍፁም ሀሳብ መውደድ ምን ማለት ይመስላችኋል? ባልንጀራን እንደ እራስ መውደድስ ምን ማለት ይመስላችኋል?*
- ባልንጀራው ማን እንደሆነ ሊያሳየው ስለ ፈለገ ኢየሱስ ታሪክ መናገር ጀመረ። አንድ ሰው ከእየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ እየተጓዘ ነበር። በመንገድ ላይም ሳለ ሌቦች አግኝተው ደበደቡት፣ ያለውንም ሁሉ ዘርፈውት ጥለውት ሄዱ። ***(ሉቃስ 10: 29-30)*** *የዚህ ሰው ጉዞ መጥፎ አጋጣሚ ሆነበት! ለልጆቹ ካርታን በማሳየት እየሩሳሌምና ኢያሪኮ የት እንዳሉ ማውጣት ይችላሉ።*
- ሶስት ሰዎች በአንድ አይነት መንገድ አለፉ። የመጀመሪያው ሰው ካህን ነበር። የወደቀውን ሰው ተመልክቶ ገለል ብሎ አለፈ። ሁለተኛው ሰው ሌዋዊ (ቤተ-መቅደስ ውስጥ የሚሰራ ሰው) ነበር። ጠጋ ብሎ የተጎዳውን ሰው ተመለከተው ምንም ሳይረዳውም ትቶት ሄደ። ***(ሉቃስ 10: 31-32)***
- ሶስተኛው ሰው ሳምራዊ ነበር። (አይሁዶችና ሳምራዊዎች አይቀራረቡም።)ወደ ተጎዳው ሰው ጠጋ ብሎ እርዳታ አደረገለትና በአህያው ላይ ጭኖ ወደ እንግዶች ማረፊያ ወሰደው። ለሊቱን ሲጠብቀው ቆይቶ ጠዋት ላይ ለእንግዳ ማረፊያው ጠባቂ የተጎዳውን ሰው እንዲንከባከበው ሁለት ሳንቲሞችን ሰቶት ሄደ። ***(ሉቃስ 10: 33-35)***
- ኢየሱስ ታሪኩን ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ እንደዚህ ብሎ ጠየቃቸው "ከሶስቱ የትኛው ነው ጥሩ ባልንጀራው?" ሰውየውም ደግ ያደረገለት ሰው እንደሆነ መለሰ። ኢየሱስም ይህን ተመሳሳይ ስራ እንዲሰራ ነገረው። ***(ሉቃስ 10: 36-37)***
- *ተወያዩ፡ ለምንተዋወቃቸው ሰዎች ደግ ልንሆንባቸው የምንችላቸውን መንገዶች ጥቀሱ? ለሰዎች ደግ መሆን ከባድ ነው? ጌታ ኢየሱስ ደግ ለሆኑልን ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰው ደግ መሆን እንዳለብን ይናገራል። ተወያዩ፡ ኢየሱስ ለእኛ ልክ እንደ ደጉ ሳምራዊ የሆነበትን መንገዶች ልትናገሩ ትችላላችሁ? (አዳኛችን፣ ረዳታችንና ጓደኛችን ሊሆን ይፈልጋል)።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**
**አሳዩ:** ስዕል፡-: የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ

**የመማር ጊዜ**

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ሉቃስ 10: 27 አስተምሩ።

**የክለሳ ጊዜ**

ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:

- ኢየሱስ የተናገራቸው ታሪኮች ምንድን ነው ሚባሉት?
- በመንገድ ላይ ያለው ሰው ወዴት እየሄደ ነበር?
- ምንድን ነው የደረሰበት?
- ምን ያህል ሰዎች አልፈውት ሄዱ?
- የትኛው ሰው ነው ሊረዳው የቆመው?
- ምንድን ነው ያደረገው?
- ለቤቱ ጠባቂ ስንት ሳንቲም ነበር የሰጠው?
- ኢየሱስ ታሪኩ ካለቀ በኋላ ለሰውየው ምንድን ነው ያለው?

## ለ5 ታሪክ 2

**የጠፋው በግ - ይህ ታሪክ ኢየሱስ ምን ያህል እንደሚያስብልን የሚያሳይ ነው።**

| | |
|---|---|
| | ***የምንማረው:***<br>• እኛ ልክ እንደጠፋው በግ ነን ብዙ ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን አድርገናል።<br>• ኢየሱስ ልክ እንደ መልካሙ እረኛ ነው ሁሌም እኛን ሊያገኘን ይፈልጋል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 10: 11***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 15: 1-7*** |
| *መግቢያ* | አወያዩ፡ ጠፍታችሁ ታቃላችሁ? እንዴት ነበር የተፈጠረው? ምን ነበር የተሰማችሁ? ማን አገኛችሁ? ስትገኙ ምን ተሰማችሁ?<br>የዛሬው ታሪክ አንድ በግ ስለ ጠፋበት እረኛ እንደሆነ ለተማሪዎች ተናገሩ።<br>አንድ እረኛ በግ ለመጠበቅ ምን ምን ማድረግ እንዳለበት ጠይቋቸው። (ማብላት፣ መጠበቅ፣ መንከባከብ ወዘተ)<br>አብዛኛውን ጊዜ በጎች ተላይተው ሄደው እንደሚጠፉ አስረዱ። |
| የማስተማር ጊዜ | • *አንድ ቀን ቀራጮች እና ኃጢአተኞች ኢየሱስን ለመስማት መጡ። ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ስለ ተቀበለ አንዳንድ ሰዎች ማጉረምረም ጀመሩ። በማጉረምረማቸው ስላልተደሰተ አንድ ታሪክ መናገር ጀመረ።* ***(ሉቃስ 15: 1-3)*** *ኢየሱስ ሁሉም ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመጡ እንደሚፈልግ ለልጆቹ አስረዱ። ማንም ቢሆኑም ምንም ጥፋት ቢያጠፉም እንኳን ችግር የለበትም።*<br>• 100 በጎች ስለ ነበሩት እረኛ ታሪክ ተናገረ። አንድ ቀን አንዱ በግ ጠፋ። እረኛውም ሌሎቹን ትቶ የጠፋውን አንዱን በግ ለመፈለግ ወጣ። እስኪያገኘው ድረስ ደስተኛ አልነበረም። ***(ሉቃስ 15: 4)***<br>• *መጽሐፍ ቅዱስ እኛ ልክ እንደ ጠፋው በግ መሆናችንን እንደሚናገር ለልጆቹ ተናገሩ። ጌታ ኢየሱስ መልካሙ እረኛ ነው። ሊያገኘንና ሊንከባከበን ይፈልጋል። ኢየሱስ እንክብካቤውን ሚያሳይበትን መንገዶች ልጆቹን ጠይቁ። መፃፍ ትችላላችሁ በተጨማሪም ለአሳቢነቱ ማመስገን እንዲችሉ ልጆቹን አበረታቱ። (ለእኛ አሳቢነቱን ያሳየበት ትልቁ መንገድ ህይወቱን ለእኛ መስጠቱ መሆኑን የሚያወራውን ነጥብ ልታሰምሩበት ትችላላችሁ።)*<br>• በመጨረሻ በጉን ሲያገኘው ደስተኛ ሆነ። ወደ ላይ አንስቶ ትከሻው ላይ አስቀመጠውና ተሸክሞት ወደ ቤት ይዞት ተመለሰ። ቤት ሲደርስ ጓደኞቹንና ጎረቤቶቹን ሁሉ ጠራና ሰበሰባቸው ምክንያቱም የጠፋውን በግ አግኝቶታል። ***(ሉቃስ 15: 5-6)***<br>• *የጠፋው በግ ሲገኝ እረኛው በጣም እንደተደሰተው ሁላ እኛም ለኃጢአታችን ይቅርታ ስንጠይቅና በኢየሱስ ስንታመን በሰማይ ታላቅ ደስታ እንደሚሆን ለልጆቹ ተናገሩ። ታሪኩን እንዳይረሱት ለማድረግ ድራማ ልትሰሩበት ትችላላችሁ። በጉ ሲጠፋ፣ እረኛው ሊፈልገው ሲወጣ፣ አገኝቶት ከጓደኞቹ ጋር ሲደሰት።*<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:** ስዕል፡- - የጠፋው በግ ምሳሌ |
| የመማር ጊዜ | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ዮሐንስ 10: 11*** አስተምሩ። |
| የክለሳ ጊዜ | ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:<br>• አንዳንድ ሰዎች ለምንድን ነው ደስተኛ ያልነበሩት?<br>• እረኛው ስንት በጎች ነበሩት?<br>• ስንት ነበር የጠፉት?<br>• እረኛው ምን ነበር ያደረገው?<br>• በጉን እንዴት ተሸክሞ ነው ወደ ቤት ያመጣው?<br>• ቤት ሲደርስ ምንድን ነው ያደረገው?<br>• በበጉ የተመሰለው ማነው?<br>• በእረኛው የተመሰለው ማነው? |

## <u>ለ5 ታሪክ 3</u>
## የጠፋው ልጅ - ይህ ታሪክ ትክክል ያልሆነ ነገር አድርጎ ስለ መጸጸት ነው።

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው:**<br>• እግዚአብሔር ላደረግናቸው ትክክል ላልሆኑ ነገሮች ይቅርታ እንድንጠይቅ ይፈልገል።<br>• እግዚአብሔር ሁሌም ቢሆን ይቅርታ ብንጠይቅ ይቅር ሊለን ዝግጁ ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሉቃስ 15: 24***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ሉቃስ 15: 11-24*** |
| *መግቢያ* | *ይቅር ማለት እንዴት እንደሆነ ተማሪዎች እንዲረዱ አጭር ታሪክ ንገሯቸው። ለምሳሌ-አንድ ቀን ያኔት እና ሳሚ እየተጫወቱ ነበር። ሳሚ በሚፈልገው ኳስ ያኔት መጫወት ጀመረች። ሳሚ ተናደደና ኳሱን ከቀማት በኋላ መትቶ ጣላት። ያኔት ማልቀስ ጀመረች።*<br>*ተወያዩ: ያኔት ለምንድን ነው የምታለቅሰው? ሳሚ ምን ማድረግ ያለበት ይመስላችኋል? ያኔት ይቅር ማለት ያለባት ይመስላችኋል?*<br>የዛሬው ታሪክ ስለ ይቅርታ ማድረግ እንደሆነ ለልጆች ተናገሩ። |
| የማስተማር ጊዜ | • ኢየሱስ ሌላ ታሪክ ተናገረ። ሁለት ወንድ ልጆች ያሉት አንድ ሰው ነበረ። ትንሹ ልጅ የእርሱ ድርሻ የሆነው ገንዘብ እንዲሰጠው አባቱን ጠየቀ። አባትየውም ድርሻውን ሰጠው። አባትና ልጅ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ተወያዩ። ***(ሉቃስ 15: 11-12)***<br>• ከትንሽ ቆይታ በኋላ ልጁ ሻንጣውን ይዞ ወደ እሩቅ ቦታ ሄደ። ባለበት ቦታ በመጥፎ ነገሮች ብሩን ጨረሰ። ከዚያም በሀገሩ ላይ ረሀብ ሆነ። ልጁ ምንም ብር አልቀረውም በዛ ላይ ደግሞ ምንም እርዳታ ሚጠይቀውም ሰው አልነበረም። ስለዚህ አሳማዎችን መጋቢ ሆኖ ስራ ተቀጠረ። አንዳንዴ በጣም ከመራቡ የተነሳ የእንስሳቱን ምግብ ለመብላት ይመኛል። ***(ሉቃስ 15: 13-16)*** *ተወያዩ: ምንም ነገር እንደሌለው ሲያስብ ልጁ ምን የሚሰማው ይመስላቸዋል? ምን ማድረግ የነበረበት ይመስላችኋል?*<br>• አንድ ቀን ስለ ቤት ማሰብ ጀመረ። ሰራተኞቹ እንኳን የሚበሉት በቂ ምግብ እንደነበራቸው ትዝ አለው። ወደ አባቱ ቤት ለመመለስና ይቅርታ ጠይቆ ከሰራተኞቹ እንደ አንዱ ለመሆን ሊጠይቀው ወሰነ። ***(ሉቃስ 15: 17-19)*** *ተወያዩ: ልጁ ይቅርታ የሚገባው ይመስላችኋል? አባቱ ይቅርታ የሚያደርግለትስ ይመስላችኋል?*<br>• ወደ ቤቱ ለመሄድ ተነሳ። አባቱ እየመጣ ሲያው ገና ሩቅ ነበረ። አባቱ እየሮጠ ሄደና ሳመው። ልጁ ይቅርታ መጠየቅ ጀመረ ነገር ግን አባትየው አስቆመው። ሰራተኞቹን ጠርቶ ምርጥ የሆነውን ልብስ፣ ቀለበትና ጫማ እንዲያመጡ አዘዘና ልጁ መመለሱን ምክንያት በማድረግ ትልቅ ድግስ አዘጋጀ። ***(ሉቃስ 15: 20-24)***<br>• *ተወያዩ: ልክ ወደ ቤቱ ሲመለስ ልጁ ምን የተሰማው ይመስላችኋል? እኛ ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን ስላደረግን ልክ እንደጠፋው ልጅ እንደሆንን አስረዱ። እግዚአብሔር ልክ እንደ አባትዬው ነው። ወደ እርሱ ቀርበን ይቅርታ እንድንጠይቀው ይፈልጋል። ተወያዩ: ይቅርታ ጠይቃችሁ ግን አልሰማ ብለዋችሁ ወይንም ይቅርታ አላደርግም ተብላችሁ ታቃላችሁ? እግዚአብሔር ሁሌም ቢሆን እንደሚሰማንና ይቅርታ ከጠየቅነውም ይቅርታ እንደሚያደርግልን ለልጆች ንገሯቸው።*<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**እሳዬ:** ስዕል፦: አባካኙ ልጅ |
| የመማር ጊዜ | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ሉቃስ 15: 24*** አስተምሩ። አባትየው ልጁ ላይ ምን እንደተፈጠረ እንዳላወቀ እና የሞተ መስሎት እንደነበር አስረዱ። አሁን ግን ስለተመለሰ ጤነኛና የእውነት በህይወት አለ። |
| የክለሳ ጊዜ | ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:<br>• ሰውየው ምን ያህል ልጆች ነበሩት?<br>• ታናሹ ልጅ አባትየውን ምን ነበር የጠየቀው?<br>• ልጁ በብሩ ምንድን ነው ያደረገው?<br>• ምን አይነት ስራ ነው የተቀጠረው?<br>• በመቀጠል ምን ለማድረግ ወሰነ?<br>• አባትየው ልጁ እየመጣ እንደሆነ ሲያይ ምንድን ነው ያደረገው?<br>• አባትየው ለልጁ ምን ነበር የሰጠው?<br>• ታሪኩ ላይ ያለው አባት እንደማን ነበር? |

# <u>ለ5 ታሪክ 4</u>

## ዘሪው - ይሄ ታሪክ በእግዚአብሔር ቃል ምን ማድረግ እንዳለብን ነው።

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው:**<br>• መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው።<br>• እግዚአብሔር ልክ እንደ ለም መሬቱ አፈር እንድንሆንና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የነገረንን ነገሮች እንድናምን ይፈልጋል፡<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማርቆስ 4: 20***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ማርቆስ 4: 1-20*** |
| *መግቢያ* | ተወያዩ፡ አትክልት ለማሳደግ ሞክራችሁ ታውቃላችሁ? ምን ነበር ያሳደጋችሁት? አትክልቱ ለማደግ ምን ምን ነበር ያስፈለገው? ጠንካራ አትክልት ሆኖ ነበር ያደገው ወይንስ ሞተ? ወይንም በትናንሽ ቡድን በመሆን የተለያዩ አይነት ዘሮችን አሳዩ።<br>የዛሬው ታሪክ ስለ አንድ ተክል ለማሳደግ ስለሚሞክር ገበሬ እንደሆነ አውሩ። |
| **የማስተማር ጊዜ** | • በጣም ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ለመስማት መጡ። በጣም ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ ስለ ተሰበሰቡ እርሱ በባህር ላይ በታንኳ ገብቶ ተቀመጠ። ሌላ ታሪክም አስተማራቸው። ***(ማርቆስ 4: 1-2)*** *ተወያዩ፡ ለምን ይመስላችኋል ሁሉም የኢየሱስን ታሪክ ለመስማት የፈለገው? በዚያ ጊዜ ብትኖሩ ኖሮ ትምህርቱን መስማት ምትፈልጉ ይመስላችኋል?*<br>• አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ። ዘሩ አራት የተለያየ አይነት መሬት ላይ ወደቀ። አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀና ወፎች መጥተው በሉት ስለዚህ ምንም አላደገም። ሌላውም በጭንጫ ላይ ወደቀና ጥልቅ መሬት ስላልነበረ ቶሎ ደረቀ። ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፣ እሾሁም ወጣና አነቀው። ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀና አድጎ ጥሩ ፍሬ ሰጠ። ***(ማርቆስ 4: 3-9)*** *በዚህ ታሪክ ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ለተማሪዎች ንገሩ። ተወያዩ፡ የእግዚአብሔር ቃል ምን ይመስላችኋል? የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቀዱስ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ከፈለግን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዳለብን አስረዱ።*<br>• ኢየሱስ ምሳሌውን ማስረዳት ቀጠለ። ቃሉም ሲዘራ በመንገድ ዳር የወደቁት በሰሙት ጊዜ ሰይጣን ወዲያው መጥቶ በልባቸው የተዘራውን ቃል ይወስደዋል። በጭንጫ ላይ የተዘሩት ቃሉን ሰምተው ወዲያው በደስታ ይቀበሉታል፣ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት ከሆነ ግን ወዲያው ይሰናከላሉ። በእሾህም የተዘሩት የዚህን አለም ሀሳብና የሀብት ማታለል ተይዘው ይወድቃሉ። ዘሩ በመልካም መሬት ላይ ሲወድቅ ልክ ሰዎች ቃሉን ሰምተው ተቀብለው ጠንካራ ክርስቲያኖች ወደ መሆን ሲያድጉ ነው። ***(ማርቆስ 4: 13-20)*** *እግዚአብሔር እኛ ልክ እንደ መልካሙ አፈር እንድንሆንና በቃሉም እንድናምን ይፈልጋል። ተወያዩ፡ እንዴት ነው እንደ መልካሙ አፈር ልንሆን የምንችለው?*<br>• *ተወያዩ፡ እስከ አሁን ከተማርናቸው ምሳሌዎች ውስጥ ለእናንተ ምርጡ የትኛው ነበረ? ለምንድን ነው የወደዳችሁት? የተማራችሁትስ በጣም ጠቃሚ ነጥብ ምን ነበር?*<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ**: ስዕል፦:የዘሪው ምሳሌ ። አንዳንድ ዘሮችንም ማሳየት ትችላላችሁ ለምሳሌ፡ ስንዴ። |
| **የመማር ጊዜ** | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ማርቆስ 4: 20*** አስተምሩ። ልጆቹ ጥቅሱን እንዲይዙት ለመርዳት ምልክቶችን መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ-መዝራት* መዝራትን ለመግለፅ፣ መስማት* ጆሮአችንን በእጃችን መከለል፣ መቀበል* ወደ ልባችን በማመልከት፣ ማፍራት* እጃችንን አንድ ላይ ወደላይ በማንሳት። ቁጥሮቹን አንድ ላይ ልንፅፋቸው እንችላለን። |
| **የክለሳ ጊዜ** | ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ፡<br>• ኢየሱስ ሰዎቹን ሲያስተምር የት ነበረ?<br>• ገበሬው ምን ነበር ያደረገው?<br>• የመጀመርያው መሬት ምን አይነት ነበር?<br>• ሁለተኛው መሬት ምን አይነት ነበር?<br>• ሶስተኛው መሬት ምን አይነት ነበር?<br>• አራተኛው መሬት ምን አይነት ነበር?<br>• ዘሩን ለማሳደግ ምርጡ መሬት የቱ ነበር?<br>• ዘሩ ምንን ነው ሚወክለው? |

# <u>ለ6 ታሪክ 1</u>
## ትንሹ ህልመኛ - ይሄ ታሪክ ስለ ዮሴፍ ህልሞች ነው።

**የምንማረው:**
- ዮሴፍ ስለ ወደፊቱ የሚያስገርሙ ህልሞች አይቷል።
- እግዚአብሔር ለዮሴፍ ህይወት እቅድ ነበረው ለእኛም ህይወት እቅድ አለው።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 37: 8***
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዘፍጥረት 37: 1-11***

### *መግቢያ*

ዮሴፍ አስራ አንድ ወንድሞች ነበሩት። ተማሪዎች ስለ እህቶች እና ወንድሞቻቸው እንዲያወሩ እድል ስጡ። ስንት ነው ያላቸው?
በእንደዚህ አይነት ትልቅ ቤተሰብ ውስጥ ማደግ ምን ሊመስል እንደሚችል ተወያዩ።

### የማስተማር ጊዜ

- የዮሴፍ አባት ያዕቆብ በከንዓን ይኖር ነበር። ዮሴፍ 17 አመቱ ነበር። የአባቱን በግ በመጠበቅ ወንድሞቹን በእረኝነት ያግዛል። አንድ ቀን ትክክል ያልሆነ ነገር ሲያደርጉ ያያቸውና ለአባቱ ይናገራል። ***(ዘፍጥረት 37: 1-2)***
- ዮሴፍ ለያዕቆብ የእርጅና ልጁ ስለሆነ ከሌሎቹ አስበልጦ ይወደዋል። እስራኤል (ያዕቆብ) ለዮሴፍ የሚያምር ባለብዙ ቀለም ኮት ሰራለት። የዮሴፍ ወንድሞች ይሄን ሲያዩ በጣም ተናደዱ። ጠሉት! ***(ዘፍጥረት 37: 3-4)*** *“መቅናት” የሚለውን ቃል ከልጆቹ ጋር ተወያዩበት። መቅናት ምን ማለት ነው? ቀንታችሁ ታቃላችሁ? ለምን ይመስላችኋል ወንድሞቹ ዮሴፍን የሚቀኑበት?*
- ዮሴፍ ህልም አለመ። ያለመውም በእርሻ መካከል ከወንድሞቹ ጋር ነዶ እያሰረ እያለ የእርሱ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች የወንድሞቹ ነዶዎች ግን ወድቀው ሰገዱለት።
- *ይህ ህልም ለዮሴፍ ልዩ ትርጉም እንዳለውና ስለወደፊቱም እንደሚናገር ለተማሪዎች አስረዱ። ልጆች የህልሙን ትርጉም እንዲገምቱ እድል ስጡ።* በህልሙና በተናገረው ነገር ምክንያት ወንድሞቹ ይልቁንም ጠሉት። ***(ዘፍጥረት 37: 5-8)***
- ዮሴፍ ተመሳሳይ ትርጉም ያለው ሌላ ህልም አለመ። በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ፀሀይ፣ጨረቃንና አስራ አንድ ኮከቦች ሲሰግዱለት ነው ያየው። አሁን አባቱን ጨምሮ ሁሉም ተናደዱበት። አባቱ እንደዚህ አለው “በውኑ እኔና እናትህ ወንድሞችህም መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?” ***(ዘፍጥረት 37: 9-10)***
- የዮሴፍ ወንድሞች የባሰ እየቀኑበት መጡ አባቱ ግን ስለ ህልሙ ማሰብ ቀጠለ። ***(ዘፍጥረት 37: 11)*** *ልጆቹ ዮሴፍ ወደፊት ምን ሊገጥመው እንደሚችል ሀሳብ እንዲሰጡ ጠይቁ። (የህልሙ ትርጉም ዮሴፍ ወደፊት በወንድሞቹ ላይ መሪ እንደሚሆን ይናገራል።) እግዚአብሔር ከጅምሩ አንስቶ ለዮሴፍ ህይወት እቅድ እንደነበረው ልጆቹን አስታውሱ። እግዚአብሔር ለእኛም ህይወት እቅድ አለው።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**
**አሳዩ:** ስዕል፡- ዮሴፍ እና ህልሞቹ

### የመማር ጊዜ

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ዘፍጥረት 37: 8*** አስተምሩ። የዮሴፍ ወንድሞች የህልሙን ፍቺ ተረድተውት እንደነበር አስረዱ። በእርሱም ይቀኑና ይጠሉት ነበር።

### የክለሳ ጊዜ

ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ፡
- በዚህ ታሪክ የዮሴፍ እድሜ ስንት ነበር?
- ያዕቆብ ለዮሴፍ የሰጠው ስጦታ ምን ነበር?
- የዮሴፍ ወንድሞች ለምን ቀኑበት?
- ቅንዓት ምንድን ነው?
- መቅናት ትክክለኛ ነገር ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
- ዮሴፍ በመጀመሪያው ወይም በሁለተኛው ህልሙ ስለምንድን ነው ያለመው?
- የዮሴፍ ህልም ምን ነበር ትርጉሙ?
- ከመጀመርያው ጀምሮ የዮሴፍን የህይወት እቅድ ያቀደው ማን ነበር?
- ልጆቹ የዮሴፍን ኮት በስዕል ስለው 12 ቦታ በመቆራረጥ መገጣጠም መስራትም ይችላሉ። ከለር ወረቀት በእያንዳንዱ ላይ ይለጥፉ። በመጨረሻም ሁሉንም መገጣጠም ይቻላል።

## ለ6 ታሪክ 2

**የተጠላው ወንድም - ይህ ታሪክ ዮሴፍ በወንድሞቹ ስለመሸጡ ነው።**

**የምንማረው:**

- ዮሴፍ በወንድሞቹ ለባርነት ተሸጠ።
- ኃጢአታችንን ከእግዚአብሔር ልንደብቅ አንችልም።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘኍልቁ 32: 23***
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዘፍጥረት 37: 12-36***

***መግቢያ***

ተማሪዎቹ ቤት ውስጥ ለወላጆቻቸው የሚታዘዙ ወይንም ስራ የሚሰሩ ከሆነ ጠይቋቸው።ያለፈውን ቀን ታሪክ አስታውሱ። የዮሴፍ ወንድሞች ለምን ነበር ዮሴፍን የሚጠሉት? በዛሬው ታሪክ ላይ ያዕቆብ ዮሴፍን በእረኝነት ላይ የነበሩትን ወንድሞቹን እንዲያይ ይልከዋል። ***(ዘፍጥረት 37: 12-17)***

***የማስተማር ጊዜ***

- ዮሴፍ እየመጣ ወንድሞቹ አዩት። በጣም ከመጥላታቸው የተነሳ ሊገድሉት ተማከሩ። ከዛ በኋላ ህልሙ ምን ይሆናል? ዋሽተው ለአባታቸው አውሬ እንደበላው ሊናገሩ ነበር። ***(ዘፍጥረት 37: 18-20)*** *ወንድሞቹ ኃጢአታቸውን ደብቀው መቼም ማንም የማያውቅባቸው መስሏቸው ነበር። እግዚአብሔር የምናደርጋቸውን ትክክል ያልሆኑ ነገሮች ሁሉ ያውቃል።*
- ሮቤል የዮሴፍ የመጀመርያ ወንድም ይህን እንዳያደርጉ አስቆማቸው።ይልቁንም ወደ ጉድጓድ እንዲወረውሩት ነገራቸው። እሱ በኋላ መጥቶ ሊያድነው አስቦ ነበር። ***(ዘፍጥረት 37: 21-22)***
- ዮሴፍ ሲደርስ ብዙ ቀለም ያለውን ኮቱን አውልቀው ወደ ባዶ ጉድጓድ ወረወሩት። ***(ዘፍጥረት 37: 23-24)***
- ትንሽ ከቆዩ በኋላ የሆኑ ሰዎች አለፉ። ቅመሞችን ለመሸጥ ወደ ግብፅ እየሄዱ ነበር። አንዱ ወንድማቸው ይሁዳ ብር ማግኘት ስለፈለገ ዮሴፍን ከመግደል ይልቅ ለእነዚህ ሰዎች እንዲሸጥ ሀሳብ አመጣ። ከዚያም ዮሴፍን በሃያ ብር ሸጡት። ዮሴፍ እንደ ባሪያ ለመስራት ወደ ግብፅ ተወሰደ። ***(ዘፍጥረት 37: 25-28)*** *ባርያ ምንድን ነው? አሁን ዮሴፍ ምን የሚሰማው ይመስላችኋል?*
- ወንድሞቹ የሰሩትን ለመደበቅ ሞከሩ። የዮሴፍን ኮት ወስደው የፍየል ደም ውስጥ ነከሩት። ወደ አባታቸውም ወስደው የዮሴፍ መሆኑን ጠየቁት። ያዕቆብ ኮቱን አወቀው። አንድ አውሬ አጥቅቶ ገድሎት ነው ብሎ አሰበ።ያዕቆብ በጣም አዘነ ሊፅናናም አልቻለም። ***(ዘፍጥረት 37: 29-35)***
- ከትንሽ ቆይታ በኋላ ዮሴፍ በህይወት በግብፅ ነበር። ለዘበኞቹ መሪ ለጲጢፋራ ሸጡት። ***(ዘፍጥረት 37: 36)***
- *ሁኔታው ለዮሴፍ ደስ የማይልና የሚያስጠላ ቢሆንም እንኳን እግዚአብሔር ግን ሁሉን እየተቆጣጠረ ነበር።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**
**አሳዩ:** ስዕል:- ዮሴፍ በጉድጓድ ውስጥ

***የመማር ጊዜ***

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ዘኍልቁ 32: 23*** አስተምሩ። ልጆቹ የ "ኃጢአት" ን ትርጉም እንደተረዱና መቀጣትም ይገባቸው እንደነበር እንደሚያውቁ እርግጠኛ ሁኑ። እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ሁሉ እንደሚያውቅ እና ለኃጢአትም ቅጣት እንደሚያስፈልግ አስረዱ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው የኃጢአትን ቅጣት ለማስወገድ እንደሆነ ለልጆቹ አስታውሱ።

***የክለሳ ጊዜ***

ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:

- በዛሬው ታሪክ መጀመርያ ላይ ያዕቆብ ዮሴፍን ምን እንዲያደርግለት ነው የጠየቀው?
- የዮሴፍ ወንድሞች ምን ሊያደርጉ ነው የተማከሩት?
- የትኛው ወንድማቸው ነው ዮሴፍን እንዳይገሉት ነገር ግን ጉድጓድ ውስጥ እንዲጥሉት ያዘዛቸው?
- ዮሴፍ የተሸጠው በምን ያህል ብር ነው?
- ወንድሞቹ ጥፋታቸውን እንዴት ነበር የሸፈኑትት?
- ያዕቆብ ዮሴፍ ምን ሆኗል ብሎ ነው ያሰበው?
- ዮሴፍ ላይ ምን እንደደረሰ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?
- እግዚአብሔር ከዚህ ቀጥሎ ለዮሴፍ ያቀደው ነገር ምን ይመስላችኋል?

## ለ6 ታሪክ 3

**ታማኙ እስረኛ - ይሄ ታሪክ ስለ ዮሴፍ ወደ እስር ቤት መግባት ነው።**

| | |
|---|---|
| | **የምንማረው:**<br>• ዮሴፍ በእስር ቤት ውስጥ እንኳን ታማኝ እና ጠንካራ ሰራተኛ ነበር።<br>• እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ።እርሱ መቼም አይጥለንም አይተወንም።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 39: 21***<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዘፍጥረት 39: 1-6 እና 19-23*** |
| *መግቢያ* | ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ርቀው ሄደው የሚያውቁ ከሆነ ጠይቋቸው። ምን ነበር የተሰማቸው? ዮሴፍ ለጲጥፋራ ቤት እንደ ባርያ ሲሸጥ ከቤተሰቦቹ ምን ያህል እርቆ እንደነበረ ተማሪዎችን አስታውሱ።ዮሴፍ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን ሊሰማው እንደሚችል አስቡት- ወደ ሌላ ሀገር ተወስዶ ባሪያ ለመሆን ሲሸጥ። |
| **የማስተማር ጊዜ** | • ዮሴፍን ወደ ግብፅ አምጥተውት እንደ ባርያ ለጲጥፋራ ሸጠውት ነበር። ጲጥፋራ የዘበኞች አለቃ ነበር። ጲጥፋራ ዮሴፍ ታማኝ እና ጠንካራ ሰራተኛ እንደሆነ አየ። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሆነ ስላወቀ በቤቱ ላይ ሾመው። ***(ዘፍጥረት 39: 1-4)***<br>• ጲጥፋራ ዮሴፍን ከሾመው ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ቤቱን ባረከ። ምግብ ከመብላት ውጪ ስለምንም አይጨነቅም ነበር። ***(ዘፍጥረት 39: 5-6)*** *እግዚአብሔር ዮሴፍን እየጠበቀው ከእርሱ ጋር እንደነበር ተማሪዎችን አስታውሱ።*<br>• አንድ ቀን የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ባላደረገው ነገር ከሰሰችው። ለጲጥፋራ ሄዳ ውሸት አወራችበት። ጲጥፋራም ሚስቱን አመናት። በጣም ተናዶ ዮሴፍ ምንም ሳያደርግ እስር ቤት አስገባው። ***(ዘፍጥረት 39: 19-20)*** *እግዚአብሔር ዮሴፍን ረስቶት ነበር እንዴ?*<br>• ነገር ግን አሁንም እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ሆኖ ያስብለት ነበረ። ዮሴፍ ታማኝነቱን እና ጠንካራ ሰራተኛነቱን ቀጠለ። የእስር ቤቱ ጠባቂም በእስረኞቹ ላይ ሾመው። ዮሴፍ በእስር ቤት ውስጥ ምንም ነገር ሲሰራ እግዚአብሔር ያሳካለት ነበር። ***(ዘፍጥረት 39: 21-23)***<br>• *በዚህ ታሪክ ውስጥ ዮሴፍ ያሳያቸውን መልካም ብቃቶች አጢቃሉ። እግዚአብሔርን መከዳት ለዮሴፍ በጣም ቀላል ነበር ። ነገር ግን ዮሴፍ እግዚአብሔርን ማስደሰት ቀጠለ። እግዚአብሔር ወደፊት ለሚኖረው ሀላፊነት ዮሴፍን እያዘጋጀው ነበር። ዮሴፍን አልረሳውም መቼም ደግሞ አይጥለውም።*<br><br>**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**<br>**አሳዩ:** ስዕል፡- ዮሴፍና የጲጥፋራ ሚስት |
| *የመማር ጊዜ* | አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***ዘፍጥረት 39: 21*** አስተምሩ። የእግዚአብሔር እቅድ አንዳንዴ ለእኛ ከባድ ሚሆንበት ጊዜ ሊኖር እንደሚችል አስረዱ። ምንም ቢሆን ግን እግዚአብሔር ስለሚወደን በዚያ ሰዓትም ለኛ መልካም ነው። |
| የክለሳ ጊዜ | ታሪኩን ለመከለስ ያክል ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቁ:<br>• ዮሴፍ ወዴት ሀገር ነው የተወሰደው?<br>• ዮሴፍን ማነው የገዛው?<br>• የጲጥፋራ ስራ ምን ነበረ?<br>• ጲጥፋራ ዮሴፍን ለምን ነበር በቤቱ ላይ የሾመው?<br>• ለምን ነበር ዮሴፍን እስር ቤት ያስገቡት?<br>• ዮሴፍ እስር ቤት መግባት ይገባው ነበር?<br>• ከዮሴፍ ጋር ማን ነበረ እየረዳው ስራው ሁሉ እንዲሳካለት ያደረገው?<br>• እግዚአብሔር ለምን ይመስላችኋል ዮሴፍ እስር ቤት እንዲገባ የፈቀደው? |

# <u>ለ6 ታሪክ 4</u>

## አዲሱ መሪ - ይህ ታሪክ ዮሴፍ የግብፅ ንጉስ ስለመሆኑ ነው ሚያወራው።

**የምንማረው:**

- ዮሴፍ በግብፅ ምድር ሁለተኛ አዛዥ ሆኗል።
- እግዚአብሔር ለዚህ የተለየ ስራ ዮሴፍን አዘጋጅቶት ነበር።

**ቁልፍ ጥቅስ:** ***1 ቆሮንቶስ 10: 13***

**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ***ዘፍጥረት 41: 14-49***

### *መግቢያ*

ግራ ከሚያጋባ ህልም ነቅተው የሚያውቁ ከሆነ ልጆቹን ጠይቁ። ምን ነበር የተሰማቸው? በዚህ ታሪክ ላይ የግብፅ ንጉስ ፈርኦን ሁለት ግራ የሚያጋቡ ህልሞችን አይቷል። ትርጉማቸው ምን እንደሆነ ማወቅ ይፈልግ ነበር። ማን ሊረዳው ይችላል?

### የማስተማር ጊዜ

- ፈርኦን በጣም ግራ የሚያጋቡ ህልሞች ነበር ያለመው። ምን ማለት እንደሆኑ ትርጉማቸውን ማወቅ ይፈልግ ነበር። በመጀመሪያው ህልሙ ላይ ሰባት ወፍራም ላሞች ከናይል ወንዝ ሲወጡ አየ። ከዛም ሰባት የቀጨጩ ላሞች ሲወጡ አየ። የቀጨጩት ላሞች ወፍራሞቹን ላሞች ይውጧቸዋል። ነገር ግን ምንም ለውጥ አልነበራቸውም! በመቀጠልም መልካም የሆኑ ሰባት እሸቶችና በንፋስ የተመቱና የሰለቱ እሸቶች አየ። እነዚህም የሰለቱት እሸቶች ያማሩትን እሸቶች ዋጧቸው። ምን ማለት አንደሆነ ፈርኦን አስማተኞቹን ጠየቀ ነገር ግን አላወቁትም ነበር። ***(ዘፍጥረት 41: 1-8)***
- *የህልሙን ትርጉም ተማሪዎች እንዲገምቱ እድል ስጡ። ፈርኦን ህልም እንዲያይ የደረገው እግዚአብሔር ነው። መልሱንም ሊሰጥ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።*
- ፈርኦን ዮሴፍን አስጠራው። ዮሴፍን ከእስር ቤት አውጥተው ወደ ፈርኦን አመጡት። ዮሴፍ ህልሙን ለመተርጎም እግዚአብሔር እንደሚረዳው ለፈርኦን ነገረው። ***(ዘፍጥረት 41: 14-24)***
- የህልሙን ትርጉም እግዚአብሔር ለዮሴፍ ነገረው። ዮሴፍም ለፈርኦን ተናገረ። ሰባቱ ወፍራም ላሞች እና ሰባቱ ያማሩ እሸቶች ሰባት የጥጋብ አመታትን ነው የሚወክሉት። ሁሉም ብዙ የሚበላው ይኖረዋል። ሰባቱ የቀጨጩ ላሞችና ሰባቱ የሰለቱት እሸቶች ግን ሰባት የረሀብ አመታትን ይወክላሉ። ከሰባቱ የጥጋብ አመታት በኋላ ሰባት የረሀብ አመታት ይሆናሉ። የረሀቡ ዘመን የጥጋቡን ዘመን እስከረሳ ድረስ በጣም የከፋ ነው። ***(ዘፍጥረት 41: 25- 32)***
- ዮሴፍ በጥጋቡ ዘመን ለረሀቡ ዘመን የሚሆን እህል እንዲያከማቹ ፈርኦን ሰዎችን እንዲያዝ ሀሳብን ሰጠ። ፈርኦን በሀሳቡ ተስማማ። ዮሴፍ ጥበበኛ ሰው እንደሆነና እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር እንዳለ ፈርኦን ያውቀ ነበር። ስለዚህም በግብፅ ምድር ላይ ሁሉ ሾመው። በግብፅ ፈርኦን ብቻ ነበር ከዮሴፍ በላይ። ***(ዘፍጥረት 41: 33-45)***
- በጥጋብ ዘመን ዮሴፍ በግብፅ ምድር ሁሉ እየዞረ ለረሀቡ ዘመን ምግብን አከማቸ። ለሁሉም ከተማ ምግብ የሚያከማቹበት ቤቶች ነበሯቸው። የረሀቡ ዘመን ሲመጣ ሰዎቹ የሚበሉት በቂ ምግብ ይኖራቸዋል። ***(ዘፍጥረት 41: 46-49)***
- *ዮሴፍ ያለፈበትን ህይወት ልጆቹን አስታውሱ። በመንገዱ ሁሉ የእግዚአብሔር እቅድ እንደነበረ አብራሩ። እግዚአብሔር ለዮሴፍ ታማኝ ነበረ። እግዚአብሔር ዮሴፍን ትቶት አያውቅም። በመንገዱ ሁሉ አላማውን በህይወቱ ላይ እየፈፀመ ነበር። ዮሴፍ ከባድ መንገዶችን ሲያልፍ በዚያ ውስጥ እግዚአብሔር ለዚህ ስራ ዝግጁ እያደረገው ነበር። እግዚአብሔር ዮሴፍን በረሃቡ ዘመን ብዙ ሰዎችን ለማትረፍ ተጠቀመበት።*

**የትምህርት ጊዜውን ጨርሱ።**

**አሳዩ:** ስዕል፡- የፈርኦን ህልም/ የዮሴፍ በግብፅ መሪ መሆን

### የመማር ጊዜ

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ቁልፍ ጥቅሱን ***1 ቆሮንቶስ 10: 13 "እግዚአብሔር ታማኝ ነው"*** አስተምሩ። "ታማኝ" የሚለው ቃል ከላይ እንደተጠቀሰው ምን ማለት እንደሆነ ለተማሪዎች አስረዱ።

### የክለሳ ጊዜ

ታሪኩን ለመከለስ ያክል ተማሪዎችን ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው:

- ፈርኦን ዮሴፍን ለምን ነበር ያስጠራው?
- በመጀመሪያው ህልም ላሞቹ ላይ ምን ነበር የተፈጠረው?
- ህልሙን እንዲተረጉም ዮሴፍን ማነው የረዳው?
- የህልሞቹ ትርጉም ምን ነበረ?
- በመትረፍረፍ አመታት የዮሴፍ ልዩ ስራ ምን ነበር?
- እግዚአብሔር ለዮሴፍ እንዴት ነበር ታማኝ የሆነው?

## ለመምህራን የእርማት መመሪያ

### ለደረጃ 1 ትምህርቶች
- በሳምንት አንድ ገፅ (ወይንም በእያንዳንዱ ጥራዝ ሁለት ገፆች) ይሰጣቸዋል። ይህም በዋነኝነት ቀለም መቀባትና የጎደሉ ቃላት መሙላትን ይይዛል።
- በየሳምንቱ 10 ነጥብ ይሰጣል። ወይንም በወር ቢበዛ 40 ነጥብ ብቻ ይያዝላቸዋል።
- የደረጃ 1 ተማሪዎች ብዙ እንዲያነቡ ስለ ማይጠበቁ ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች/ እንዲሁም መሪዎች እርዳታ እንዲሰጧቸው ይጠበቃል።
- ለአንድ መልስ ሁለት ነጥብ ይሰጣል። እንዲሁም በእያንዳንዱ ትምህርት ለቀለም ቅብ 10 ነጥብ ይሰጣል።

### ደረጃ 2 ትምህርቶች:
- በሳምንት 2 ገፆች ወይንም ደግሞ በአንድ ጥራዝ 4 ገፆች ይሰጣቸዋል።
- ታሪኮቹ የሚገኙት በየትምህርቶቹ ውስጥ ነው። ተማሪዎች የተለያዩ ቃላትን ከየትምህርቶቹ መፈለግ፣ የቀለም ቅብ ስራ መስራትና ቁልፍ ጥቅሶችን ማሟላት ወዘተ… ይጠበቅባቸዋል።
- ልክ ትምህርቶቹ ሲጠናቀቁ በየሳምንቱ ሀያ ነጥቦ በወር ደግሞ ቢበዛ 80 ነጥቦች ሊሰጡ ይገባል።

### የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ነጥብ አሞላል

### የነጥብ አሞላል ፍንጮች
መምህራን በመጀመሪያ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ።
- እያንዳንዱን ትምህርት መገምገምና መልሶቹ ትክክል መሆን አለመኖናቸውን ምልክት ማድረግ።
- በመመሪያው መሰረት ትክክለኛውን ነጥብ መስጠት።
- ነጥብ ስንሰጥ የተለያየ አይነት ቀለም ያላቸውን ብዕሮች /እስክርቢቶዎች/ መጠቀም አለበን። ትክክል ለሆኑ መልሶች የ "⎤" ምልክት እናድርግ።
- ትክክል ላልሆኑ መልሶች ትክክለኛ መልሶቻቸውን አስቀምጡ። የፊደላት ግድፈቶች ካሉም እርማት ስጡ። ለፊደላት ግድፈት ነጥብ አይቀነስም።
- በከፊል ትክክል ለሆኑ መልሶች ነጥብ ቀንሱ።
- የወሩን ድምር ነጥብ አስቀምጡ። ይህንንም በጀርባ ገፅ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ለይ ፃፉ።

አንዳንዴ በአግባቡ ሊጋስ መሆን ያስፈልጋል። እንዲሁም ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ለማበረታታት ማንኛውንም ነገር ማድረግ አስፈላጊ ነው። በየወሩ መጨረሻ መምህራን አንድ የማበረታቻ ቃል ለተማሪዎች ቢፅፉ መልካም ነው። ይህን ለማድረግም በየትምህርቶቹ ቦታ ተዘጋጅቷል። ጥሩ የቀለም ቅብን፣ ንፅሕናን፣ ተማሪው ያስመዘገበውን ነጥብ፣ ተማሪው ምን ያህል እንደተረዳ የሚገልፁ አስተያየቶችን መፃፍ ይቻላል።

አስተያየቶች በተቻለ መጠን የተለያዩ እንዲሆኑ መጣር አለብን። ጥያቄዎች፣ አረፍተ ነገሮች፣ ምልከታዎች፣ ማበረታቻዎች ወዘተ… ይህን ልዩነት ለማሳየት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ይህ በጥልቅ ማሰብንና የተማሪዎች ፍላጎት መጠበቁን ማረጋገጥ ይጠይቃል። አንድ አረፍተ ነገር ወይንም ደግሞ ጥያቄ በየወሩ የሚደጋገም ከሆነ የሚፈለገውን ግብ ላይመታ ይችላል።

### ደረጃ 1
#### አጠቃላይ አስተያየቶች
"ኤሚ ይህን ትምህርት በመጀረሽ በጣም ደስተኛ ነኝ። እንዲሁም በትምህርቶቹ በጣም ደስተኛ እንደሆንሽ እርግጠኛ ነኝ። የቀለም ቅብሽ አስደስቶኛል። ትምህርት ቤት እየሄድሽ ነው ወይ? እስኪ ስለ ትምህርት ቤትሽ ንገሪኝ። መልስሽን በናፍቆት እጠብቃለሁ።"
"እንድርያስ! እጅግ በጣም ግሩም ስራ ነው። የሚገርም ቅብ ነው! መስመር መጠበቅ ከባድ ነበር እንዴ? አንድ ቅብ ሊያርፍበት የሚገባውን ቦታ የዘነጋኸው አይመስልህም?"

#### መንፈሳዊ አስተያየቶች
"ሳራ! ግሩም ሰራ! ኢያኢሮስ ኢየሱስ የረዳው ደስተኛ ሰው ነበር!"
"እጅግ በጣም ጥሩ መልሶች! የኢየሱስ ሞት ታሪኩ አሳዛኝ ቢሆንም ከሙታን መነሳቱ ደግሞ እጅግ አስደሳቹ ጫፍ ነው።"

### ደረጃ 2
#### አጠቃላይ አስተያየቶች
" ዮናስ፣ መልስህ ጥሩ ነው። እርግጠኛ ነኝ የት/ቤት አስተማሪዎችህ በአንተ እጅግ በጣም ደስተኞች እንደሆኑ እርግጠኛ ነኝ።"
"ብሩክ! የልደት ቀንህ እየደረሰ እንደሆነ አውቄአለሁ። ለልደትህ ልዩ ዝግጅት እያደረግህ ነው? ምንም ነገር ብታደርግ መልካም ልደት እመኝልሃለሁ።"
"ጥረትህ በጣም አስገራሚ ጥረት ነው። ትንንሽዬ ስህተቶች አሉ። ሁልጊዜም መልሶችህን እንደገና አረጋግጥ።

#### መንፈሳዊ አስተያየቶች
"በበረት ውስጥ ያለውን ሕፃኑን ኢየሱስን የቀባሽበት መንገድ አስደስቶኛል። እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም ስለ እኛ መላኩ መልካም አይደለምን?
"ቅቦችህን በጣም ወድጃቸዋለሁ! እግዚአብሔር ያለውን ነገር ባለማመኑ ዘካሪያስን ዋጋ አስከፈለው። ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል አልተጠራጠረም።"
"እጅግ በጣም አስደናቂ መልሶች! በምድረ በዳ ፊልጶስን የተገናኘው ሰው ደስተኛ ሆኖ ሄደ። ስለ ኢየሱስ መልካሙን ዜና ሰምቶ አመነ።

© Bible Educational Services 2015

www.besweb.com

Registered Charity UK 1096157